

ሳምራዊው ሰው በችግር ላይ የነበረውን ሰው እንደ ረዳ እኛም የእሱን ምሳሌ ተከትለን ወገኖቻችንን እንርዳ

# ትንሣኤ



ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ሆይ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑሻል

ዋጋው ሃምሳ ሳንቲም ቍጥር 13 ፲፱፻፹ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

ፌ.! 10/12-76

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና፣ ታሪክ ሥርዓትና ዜና ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐም ለሥራ እንነሳ የሚል ስለሆነ «ትንሣኤ» ተብሎ ተሰይሟል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ ።
በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

አዘጋጅ
ንቅዓ ጥበብ ወንድም

የስልክ ቁጥር 116646
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ

## አርእስት


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| -ሁሉም ሥራውን ያክብር | ፪ |
| -ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል | ፫ |
| -ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሶቭየት ኅብረት ተመለሱ | ፬ |
| -እንክርዳዱ ከወዴት መጣ ? | ፮ |
| -"ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት" | ፰ |
| -ሊቃውንት በትምህርታቸው ሳይሠሩበት እንዳያልፉ ምን መደረግ አለበት? | ፲ |
| -ሥራና እምነት በሴቶች ሕይወት | ፲፪ |
| -የሠራተኞች ኃይል እንዳይከፋፈል | ፲፬ |
| -ቤተ ክርስቲያንና ውለታዋ | ፲፮ |
| -ካህናቶቻችን | ፲፯ |
| -የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመንበረ ፓትርያርኩን 60ኛ ዓመት አከበረች | ፲፯ |
| -የእግዚአብሔር ሀላዌ | ፲፰ |
| -ልማድ ሃይማኖት አይደለም | ፲፱ |
| -"ወላጆች ልጆቻችሁን በሥነ ሥርዓት አሳድጉ" | ፳፩ |




የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የሁለተኛ ዓመት በዓለሢመት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም. ይከበራል



www.ethiopianorthodox.org

# "ሁሉም ሥራውን ያክብር"

ሁሉም ሥራውን እንዲያከብር የሥራን እኩልነትና ክቡርነት እንዲረዳ ለማድረግ አንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ "የቤተ ክርስቲያንን አጥር ግቢ የሚያፀዳ ሠራተኛና በመሠውያው ፊት ለፊት ቆሞ የሚቀድሰው ካህን በእግዚአብሔርም ሆነ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚሰጡት አገልግሎት እኩል ነው" ሲል ተናግሮአል ። ሊቁ እንደገለጸው የሥራ ትንሽ የለውም ሁሉም የተመደበበትን አክብሮ ለወገንና ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ከሠራ አገሩ የምትጠብቅበትን ግዳጅ ተወጥቶአል ።

ስለዚህ ነው በተለይ ኅብረተሰብአዊነትን መመሪያ ያደረጉ አገሮች "ለእያንዳንዱ እንደሥራው ለእያንዳንዱም እንደችሎታው" የሚለውን ዐቢይ አነጋገር መሠረታዊ መርሆ አድርገው የሚጠቀሙበት ። ታዲያ ሥራ ክቡር መሆኑን ተረድተው ለሀገር ብልፅግናና ለወገን ደህንነት ሲሉ ሥራቸውን አክብረው የተጣለባቸውን የሥራ ድርሻ በሚገባ የሚያከናውኑ ሠራተኞች ቁጥር ስንት ይሆን ? አንድ ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ ጥናት ቡድን "በዓለም ላይ ወደ ሥራ ከተዘረጉት እጆች ቁጥር ይልቅ ወደ ማዕድ የሚዘረጉት እጆች ቁጥር ይበልጣል" ሲል ተናግሮአል ። በእርግጥም አነጋገሩ በአሁኑ ጊዜ ዕለታዊ መፍትሔ ያልተገኘለትን ዓለም አቀፋዊ የሥራ አጥነት ችግር ይገልጻል ። ይህንንም ዓለም አቀፋዊ ችግር ለማስወገድ በተለይ ኅብረተሰባዊነትን መመሪያ ያደርጉ አገሮች ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

በኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያም ወደ ማዕድ ከሚዘረጉት እጆች ቁጥር ይልቅ ወደ ሥራ የሚዘረጉት እጆች ቁጥር የበለጠ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑ ብዙ የማያጠያይቅ ሐቅ ነው ።

ሆኖም አንዳንድ ግለሰቦች እጆቻቸውን ወደ ሥራ ከሚዘረጉ ይልቅ ምላሶቻቸውን ለነገር መጐልጐል ፣ እጆቻቸውን ወደ ማዕድ መዘርጋቱ ይቀላቸዋል የሀገር ስሜትና የወገን ፍቅር አስገድዷቸው ሌት ከቀን ለሚሠሩት ግለሰቦች የሞራል ድጋፍ በመስጠት በመልካም አርአያነታቸው መመስገን ሲገባቸው አንዳንድ የወገንና የሀገር ፍቅር ፈጽሞ የከዳቸው ነገር አንጓቾች ልዩ የሽሙጥ ስም በማውጣት እዲያ የሱን ነገር ተወው! ሠራተኛ መስሎ ለመታየትና የደመወዝ ጭማሪ ወይም ዕድገት ለማግኘት ነው እንደዚህ የሚዋትተው በማለት የነገር አሽከላ የሚተበትቡ ግለሰቦች ሥራ ፈት እጆቻቸውን በአፈጮሌነት ካባ ለመሸፈን ቢሞክሩ ፣ አላዋቂነታቸውንም ብዙ በመለፍለፍ ለመሸፈን ቢጥሩ ለጊዜው ታሪክ እስከፈቀደላቸው ተጉዘው ታሪክ መልሶ በሥራቸው ስለሚተፋቸው ብዙ አይደንቀንም የሚደንቀው የሥራውን ክቡርነት በመረዳት ሥራቸውን በሚገባ ለሚያከናውኑት እንደዚህ ዓይነቱ ስም ከተሰጣቸው ሥራ ፈቶ ነገር ሲጠመዝዝ ወሬ ሲያርቅ ለሚውለው ምድረ ዋልጌ ምን ስም ይሰጠው ይሆን ?

ከመንፈሳውያን መምህራን አንዱ ቅዱስ ጳውሎስ "ወንድሞች ሆይ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና ከናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን" ሲል ተናግሮአል ። ከሐዋርያው አነጋገር መረዳት እንደምንችለው አንዳንድ ሰዎች በሥራቸው ላይ ስንፍና ቢታይባቸው ሥራቸውን ከመበደላቸውም በላይ ራሳቸውን ለድኅነትና ለችግር ስለሚዳርጉ የሀገርና የወገን ሸክም ይሆናሉ ።

ይህም ሥራ ያከበሩትን ያህል እንደሚያከብር ያዋረዱትን ያህል ደግሞ እንዲሁ እንደሚያዋርድ ያስረዳናል በአሁኑ ጊዜ የሥራን ክቡርነት አለመረዳትና ቸልተኝነት ወሬ ማሞቅና ነገር ማሳመቅ በይበልጥ ጐልተው የሚታዩት በአብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ውስጥ ባሉ አሠሪዎችና ሠራተኞች መካከል መሆኑ ብዙ መረጃ የማያሻው ሐቅ ነው ምናልባት በዚህ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ሰዎች ጥቂቶቹ ጸሎትን እንደ ሥራ በመቁጠር ለሥራ ፈትነት ራሳቸውን ሳያጋልጡ አልቀሩም ።

አውግስጢኖስ የተባለው የነገረ መለኮት ሊቅ ጸሎት ሥራ ነው የሚለውን የጥንት ዘይቤ ሲቃወም "ሥራ ጸሎት ነው" ብሎአል ።

ሊቁ ይህንን የተናገረበት ዋናው ምክንያት አንድ ሰው ሲጸልይ ሲሰግድ ውሎ ሰዓት ሲደርስ የዕለት ምግብ እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነው ። ምግብም የሚገኘው በሥራ ስለሆነ ሁሉም ሥራውን ያክብር ለማለት ነው "ያልሠራ አይብላ" ብሎአልና ታላቁ መጽሐፍ ።

ስለሆነም አሳቤ ጸሎትን ለመቃወም አለመሆኑ እንዲታወቅልኝ እወዳለሁ ፤ ጸሎት በተወሰነ ጊዜ የሚፈጸም ስለሆነ አንድ ሰው ከሥራ በኋላ ቢጸልይ ቢዘምር የመንፈስ ደስታ ሊያገኝ ይችላል ካልሠሩ ደስታ የለም ሊቁም እንደተናገረው ሥራ ራሱ ጸሎት ነው ከሥራና ከእምነት የተለየ ጸሎት የሞተ ነውና ።

- መዘምር ካሣሁን



# ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል

ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት ። ማርያምም እንዲህ አለች ። ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች ፤ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፣የባሪያዩቱን ውርደት ተመልክቶአልና ። እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤

እምነት የደስታ ምንጭ ነው እንደሚባለው ማንኛውም ሁኔታ ሊስተካከልና ሊፈጸም የሚችለው ከእምነት የተነሣ ነው ። እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርግ ማንኛውም ነገር ይፈጸምለታል ። ያሰበው ሁሉ ይከናወንለታል ። ቅድስት ድንግል ማርያም እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ብፅዕት እንድትባል ያበቃት ከፍተኛው እምነቱዋ ነው ። እመቤታችን የልቧ ቅንነት የአንዋዋሩዋ ንጽሕና ፣ ርኅራኄዋ ፣ ታጋሺነቱዋ ፣ በጠቅላላውም ከመላው ዓለም ሴቶች ሁሉ ቅድስናዋ የጌታችን እናት እንድትሆን ስለአበቃት ንጽሕት ወቅድስት ለመባል በቅታለች ።

ስለዚህም ካላት የእምነት ፅኑነት የተነሣ ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም ባምላኬ በመድኃኒቴ ሃሴት ታደርጋለች የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና ስትል እግዚአብሔርን በምን ዓይነት የተቀደሰ እምነት እንደምታከብረው ተናግራለች ። መንፈሴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ።

አዎ በእግዚአብሔር የሚያምን የእግዚአብሔርን ትሩፋትና ስጦታ ማየት ይችላል ። በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ በእግዚአብሔር ይደሰታል ። በእግዚአብሔር የሚደሰትም እግዚአብሔር ደስ ያሰኘዋል ፤ በእግዚአብሔር የሚደሰቱ ወገኖችን እግዚአብሔር ከውርደታቸው ያከብራቸዋል ፣ ውርደታቸውንም ተመልክቶ ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላጆቹዋን በልጅነቱዋ ያጣች በቅርብ ጠያቂ ዘመድ የሌላት ተስፋዋና አለኝታዋም እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ በእግዚአብሔር ቤት የምትቀመጥ ብቸኛ ነበረች ። ግን እግዚአብሔር ትህትናዋን ፣ ቅንነቷዋን ፣ ንጽሕናዋን ተመልክቶ የእግዚአብሔር እናት እንድትሆን መረጣት ። ስለዚህም መንፈሴ በአምላኬ በመድኃኒት ሐሴት ታደርጋለች ። የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና ስትል ራሱዋን ዝቅ ዝቅ አድርጋ ይህን ላደረገላት አምላክ ከልብ የመነጨ ምስጋናዋን አቀረበች ።

ይህ ሁሉ ሊደረግላት የቻለው በእምነቱዋ ጽንአት የተነሣ ነው ። እምነት የድል መንሻ መሣሪያ ነው የሚባለውም ስለዚህ ነው። እግዚአብሔርም ያደረገላትን ድንቅ ሥራ እመቤታችን ከተመለከተች በኋላ ምን ያህል ዘለዓለማዊ ክብርን እንዳጐናፀፋት ስትመሰክር እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ስትል ለዘለዓለም ስትመሰገን የምትኖር የዘለዓለሙ ትውልድ ሁሉ ሲያመሰግናት እንደሚኖር ተረድታ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ስትል ተናግራለች ።

እነሆ በዚሁ ዘለዓለማዊ ቅዱስ ቃሏም መሠረት ትውልድ ሁሉ ሲያመሰግኑዋት ኖረዋል ፣ ወደፊትም ሲያመሰግኑዋት ይኖራሉ ።

በተለይ በኢትዮጵያ ቅድስት ድንግል ማርያም የተለየና የከበረ ምስጋና የሚቀርብላት እመቤታችንን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመውደዱ የተነሣ ነው ። ኢትዮጵያውያን እመቤታችንን የሚወዱበት አማናዊ ምክንያት አላቸው ይኸውም በኃጢአት ምክንያት ሰውና እግዚአብሔር ተጣልተው ሲኖሩ ሰውና እግዚአብሔር እንዲታረቁ ፣ እግዚአብሔርም የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብሎ የሰዎችን በደል በራሱ ሞት አስወግዶ በገዛ ደሙ የታረቀንን ክርስቶስን ያስገኘች ቅድስት ድንግል ማርያም በመሆኑዋ ነው ።

ስለዚህ ነው ብዙ ቅዱሳን ደራሲያን እመቤታችንን በሐገር የሚመስሉዋት ። ሀገር ነፃነት ፣ የክብር ፣ የመኖር ፣ በጠቅላላውም የሃብት መገኛ ስለሆነች ሀገር ከፍተኛ ክብርና የተለየ ውዴታ ይሰጣታል ። እመቤታችንም ከዘለዓለም ባርነት ወደፍጹም ነፃነት ፣ ከወራዳነት ወደታላቅ ክብር እንድንደርስ እግዚአብሔር የታረቀን በእርሱዋ ምክንያት በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ለእመቤታችን ከፍተኛ ክብርና የተለየ ፍቅር አላቸው ። አገር ከሌለ ነፃነት አይኖርም እመቤታችንም ክርስቶስን ባትወልድልን ኖሮ መንፈሳዊ ነፃነት ሊኖረን አይችልም ነበር ።

ስለዚህም በተለያዩ ጊዜያት የእመቤታችንን በዓል በተለየ መንፈሳዊ ስሜትና በደመቀ ክብር ኢትዮጵያውያን እናከብራለን ።

ከነዚህም ከእመቤታችን በዓላት አንዱና ተወዳጅም የሆነው የፍልሰታ ጾም ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ። ስትል በተናገረችው የተቀደሰ ቃል መሠረት ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወርኃ ፍልሰታ ሁሉም እንደየችሎታው ያመሰግኗታል ። ልጅ አዋቂ ብፅዕት ይላታል ። በተለይም ሕፃናት በዚህ የፍልሰታ ጾም ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ። ይጾማሉ ፣ ሥጋ ወደሙ ይቀበላሉ በየቤተ ክርስቲያኑ ተገኝተው ያስቀድሳሉ ይጸልያሉ በገጠሩም በእረኝነት ተሠማርተው የሚገኙ ሕፃናት ሲጾሙ እየዋሉ ገበሬዎች የምሳ ሰዓት መድረሱን አውቀው ምሳ እስከሚበሉ ጠብቀው ሰዓት አድርሰው ይበላሉ ገበሬዎች በሌሉበት ቦታ ያሉ ሕፃናትም ከወላጆቻቸው በተማሩት የሰዓት አቆጣጠር ጫማ ሰፍረው ሰዓት መድረሱን አረጋግጠው ይበላሉ ። ይህ ሁሉ

ተከታዩን በ፮ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሶቭየት ኅብረት ተመለሱ



ሞስኮ፦ የሴሚናሩ በዓል በተከፈተበት ጊዜ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሶቭየት ኅብረትና በፖላንድ የሚያደርጉትን ሐዋርያዊ ጉዞ ፈጽመው ሰኔ 8 ቀን 1970 ዓ.ም. ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ።

ቅዱስነታቸው ወደሶቪየት ኅብረት የሄዱት የሶቪየት ኅብረት በኅብረተሰብአዊነት መመራት ከጀመረችበት ከ1917 ዓ.ም. ወዲህ የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ መንበረ ፓትርያርክ በኅብረተሰብአዊ ኅብረተሰብእ መካከል በተሐድሶ ለመንፈሳዊ ሥራው መልካም ርምጃ ያደረገበትን ስለሚያከብር ብፁዕ ወቅዱስ ፒሜን የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ ፓትርያርክና ቅዱስ ሲኖዶስ ስለጋበዛቸው ነበር ። ቅዱስነታቸው ግንቦት 10 ቀን 1970 ዓ.ም. ከጧቱ በ3 ሰዓት ከአዲስ አበባ ተነስተው መስኮብእንደደረሱ ሽሬሜየቴቭ በተሰኘው ዓለም አቀፍ የመስኮብ አየር ማረፊያ ብፁዕ ወቅዱስ ፒሜን ከቅዱስ ሲኖዶስ አባሎች ጋር በመስኮብ የኢትዮጵያ አምባሳደር የኤምባሲው ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ተቀብለዋቸዋል ።

በማግሥቱ ግንቦት 11 ቀን 70 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው የክብር ተከታዮቻቸውን ይዘው ወደ አርሜንያ ጉዞ አድርገዋል ። ወደአርሜንያ የሄዱበትም ምክንያት ብፁዕ ወቅዱስ ባዝጌን ቀዳማዊ የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ቀደም አድርገው ቤተክርስቲያናቸውን እንዲጎበኙላቸው ጋብዘዋቸው ስለነበር የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን በዓለ ተሐድሶ ከመድረሱ በፊት ነበር የጐበኙት ። በዚህም መሠረት በየረቫን አኤሮፕላን ጣቢያ እንደደረሱ ብፁዕ ወቅዱስ ባዝጌን ቀዳማዊ ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በአርመን የሃይማኖትና የባህል ጉዳይ ሚኒስትርና ሌሎችም ከፍተኞች ባለሥልጣኖች በታላቅ ክብር ተቀብለዋቸዋል ።

በኢቸሚአዚን ገዳም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን መነኮሳት ፣ ቀሳውስት ፣ ዲያቆናት የመንፈሳዊ ኰሌጅ ተማሪዎች እየዘመሩ በሰልፍ ተቀብለዋቸዋል ስለቅዱስነታቸውም በታላቁ ገዳም (ቤተ ክርስቲያን) ጸሎት ተደርጓል ።

ለቅዱስነታቸው ጉብኝት በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ተከታዮቻቸው ገዳማትን ፣ አድባራትን አብያተ ክርስቲያናትን የታሪክ ሥፍራዎችን ሙዚየሞችን እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል።

በተለይም ለአገራቸው ነፃነትና ለሕዝባቸው ደኅንነት ሲሉ ደማቸውን ባፈሰሱት አጥንታቸውን በከሰከሱት ጀግኖች መታሰቢያ ሐውልት ስር የአበባ ጉንጉን አኑረዋል፣ የሁለቱም አብያተ ክርስቲያን መሪዎች አጭር ጸሎተ ፍትሐት (ሙታን) አድርሰዋል። በዚህም ሥርዓተ ጸሎት የአርመን ሪፐብሊክ የሃይማኖቶችና የባህል ምክትል ሚኒስትር ተገኝተዋል ።

ቀጥሎም የሶቭዬት ኅብረት አርመን ምክር ቤት ዋና ሊቀ መንበርና የመንግሥት ባለሥልጣኖች ቅዱስነታቸውን በምክር ቤቱ ተቀብለው ለአንድ ሰዓት ያህል አነጋግረዋቸዋል ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ፍቅር ገልጸውላቸዋል ። በሶቭዬት ኅብረት በሃይማኖት ፣ በጎሣ ፣ በቋንቋ ፣ ልዩነት እንደማይደረግ አውስተው እማኞችም እምነታቸው የሚያዘውን ሥርዓት ለመፈጸም ሙሉ መብት እንዳላቸው በሰፊው በማብራራት አስረድተዋል ።

ቅዱስነታቸው በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር ድንበሩን ለመጠበቅ ፣ ረሀብን ድንቁርናን በሽታን ለማስወገድ በመታገል ላይ መሆኑን በሰጡት መልስ ላይ አብራርተዋል ።

በጉብኝቱ ፍጻሜ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ የጋራ መግለጫ አውጥተዋል ።

በመግለጫው ላይ ከወጡትም የስምምነት ሃሳቦች ላይ የሚከተለው ዐበይት ነጥቦች ይገኙባቸዋል ። ከነጥቦቹም ጥቂቶቹ

ሀ/ 1ኛ/ የኢትዮጵያ
2ኛ/ የግብፅ፣
3ኛ/ የአርመን ፣
4ኛ/ የሶርያ ፣
5ኛ/ የሕንድ ማኅበረ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በቅርብ ጊዜ ተገናኝተው ስለአብያተ ክርስቲያኖቻቸው መንፈሳዊ እድገት ለመወያየት ወስነዋል ። ጋባዥም የምትሆነው የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ናት ።

ለ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን ወደ አርመን መጥተው በመንፈሳዊ ኰሌጅ ከፍተኛ ትምህርት እንዲቀጥሉ

ሐ/ የጉብኝት ልውውጥ እንዲደረግና ሁለቱም አብያተ ክርስቲያን በጋራ የቤተ ክርስቲያናቸውን ሥርዓት እንዲጠብቁ በነዚህና በሌሎችም ነጥቦች ላይ ከተነጋገሩ በኋላ ፈርማቸውን አኑረዋል ። በዚህ አኳኋን ግንቦት 14 ቀን 1970 ዓ.ም. የጉብኝቱ መርሐ ግብር ተፈጽሞ ወደ መስኮብ ተመልሰዋል ።

መ/ ግንቦት 17 ቀን 1970 ዓ.ም. ጧት የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የ60ኛ ዓመት የመንበረ ፓትርያርኩ በዓለ ተሐድሶ በታላቅ ድምቀት ተከፍቷል ። በዕለቱም በእንግድነት ከመላው ዓለም የመጡ ፓትርያርኮችና የፓትርያርክ መልእክተኞች ተገኝተዋል ።

በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ ብፁዕ ወቅዱስ ፒመን የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ ፓትርያርክ የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል ። በ30 ገጽ የሠፈረ ንግግራቸው የሩሲያን ቤተ ክርስቲያን በሬቮሉሽኑ ጊዜ የመሩና ከዚያም ወዲህ መልካም የሥራ ፍሬ ያሳዩትን የቅዱስ ቲሆንን፣ የቅዱስ ሰርግዮስንና የቅዱስ አሌክሴይን የሕይወት ታሪክና ሥራ ተጋድሎ የሚገልጽ ሲሆን በአንድ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱ በጦርነቱ ጊዜ በሕዝቧ ጋር ሆና ለአገሩ ነፃነትና ክብር ያደረገችውን ትግል የክርስቶስን ትምህርት ለማስፋፋት ፣ ሃይማኖትን፣ ለመጠበቅ እንዲቻል በመንፈሳዊ ትምህርት በኩል ያደረገችውን ርምጃ ፣ ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት ከመንግሥቷም ጋር ያላትን የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነት በሶቭዬት ኅብረት ስላለው የሃይማኖት ነፃነት ተንትነው አስረድተዋል ። በዚህም ጊዜ በሦስቱ ፓትርያርኮች መካነ መቃብር ላይ ጸሎተ ፍትሐት ተደርጓል በተለይም እንግዶቹ በዛግርስክ የሚገኘውን ታላቁን ገዳምና መንፈሳዊ አካዳሚውን እጅግ አስደናቂ የሆነ ሙዚየሙን ጎብኝተው ወደ መስኮብ ተመልሰዋል ። በዓሉ ተጀምሮ እስከተፈጸመበት ዕለት ድረስ በየዕለቱ ከመላው ዓለም የተጋበዙ የፓትርያርኮች መልእክተኞች የሰላምታ ቃል በየተራ ተናግረዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና በራሳቸውም ስም የአብያተ ክርስቲያናትን ወዳጅነት የሚያጠነክር የሰላምታ ቃል ተናግረዋል ።

ስለዓለም ሰላም ያላቸውን መልካም ምኞትም ገልጸዋል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ረሀብን ፣ በሽታን ፣ ድንቁርናን ለማስወገድ በሚጥርበት በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የውጭ ኃይሎች የሚፈጸመውን የተንኮል ተግባር በጉባዔው የተገኙት የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ልዑካን በግልጽ እንዲያውቃቸው አድርገዋል ።

ሠ/ ግንቦት 21 ቀን 1970 ዓ.ም. የበዓሉ ስነ ሥርዓት እንደተፈጸመ በሶቭዬት ኅብረት የሚገኙትን ገዳማትና አድባራት እንዲጎበኙ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ቅዱስነታቸውና ተከታዮቻቸው በፈጣን ባቡር ተሳፍረው ወደ ዩክሬይን ሪፐብሊክ ዋና ከተማ ኪቭ ተጉዘዋል ።



ቅዱስነታቸውና ተከታዮቻቸው ሊቃነ ጳጳሳት ከሜትሮፖሊት ባሲሊዮስ ከሃይማኖት ሚኒስትር ከምክትል ሚኒስትር ከውይይት በኋላ ለመታሰቢያ የተነሱት ፡

ከዚያም እንደደረሱ ብፁዕ ፊላሬት የኪብና የመላዋ ዑክራይን መትሮፖሊታን ፣ የሬፐብሊኩ የሃይማኖትና የባህል ም/ሚኒስትር ሌሎችም የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ባለሥልጣናት በባቡር ጣቢያ ተገኝተው የደመቀ አቀባበል

በ፱ኛው ገጽ ይመለከቱ





www.ethiopianorthodox.org

# ትውልድ ሁሉ

ከ፫ኛው ገጽ የዞረ

የቅዱስ መጽሐፍ ቃል የማይሻር የማይ
ለወጥ በመሆኑ እነሆም ከዛሬ ጀምሮ
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ባለች
ው አማናዊ ቃል መሠረት ነው።ከእመ
ቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሌ
ላ የምንማረው ቁም ነገር አለ።ይኸውም
1ኛ/ ከንጽሕናዋ የተነሣ ለንጹሕ አገል
ግሎት አምላክን ለመውለድ ተመረጠ
ች ። እኛም በምንሠማራበት አቅጣጫ
ሁሉ የሥራ ንጽሕናችንን ብንጠብቅ
ለንጹሕ አገልግሎት እንመረጣለን ።
ያለው የንጽሕና ሥራ አምላክን መው
ለድ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ለወገን ንጹሕ
አገልግሎት ማበርከት የተቀደሰ መስዋ
ዕትነት ነውና ለከፍተኛ ቁም ነገር ያደ
ርሳል ። 2ኛ/ ከትሕትናዋ የተነሣ ዝቅተ
ኞችን በማገልገሉዋና በመርዳትዋ እን
ዲሁም ለሁሉም በመታዘዙዋ ሰውና
መላእክት እንዲያገለግሉዋት እንዲታዘ
ዙዋት ተደረገ ።

እኛም ዛሬ ሌሎችን ብናገለግል ፣ ሌ
ሎችን ብንረዳ ለሌሎች ብንታዘዝ ሌሎ
ች ይታዘዙልናል ፣ ሌሎችም ይረዱናል
ዛሬ ለማዘዝ የሚያበቃ መታዘዝ እን
ጂ ትልቅ ነኝ ማለት ብቻ አይደለምና
3ኛ/ እግዚአብሔርን በንጹሕ ልብ ከእ
ውነት በመነጨ እምነት በማመስገኑዋ
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ንጽሕት ክብር
ት እያሉ እንዲያመሰግኑዋት ፣ እንዲያ
ገለግሉዋት ፣ እንዲያወዱስዋት ተደ
ረገ ። እንዲሁም እኛ እግዚአብሔርን
ከእውነተኛ መንፈስ በመነጨ እምነት
እያመሰገን በየተሠማራንበት ሥራ ቅን
አገልግሎት ብናበረክት እግዚአብሔር
ሥራችንን ባርኮ የተሠማራንበት ሥራ
እንዲያስመሰግነን የተባረከና ወገን
የሚጠቅም እንዲሆን ያደርግልናል ።
ስለዚህ ዛሬም መልካም አድራጊዎች
ቅን አሳቢዎች በንጹሕ እግዚአብሔርን
የሚያመሰግኑ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘን
ንድ እውነተኛ ዋጋቸውን አያጡም ።
እግዚአብሔር ያን ጊዜም ዛሬም ያው
ነው አይለወጥም ደግ አድራጊ ቢለግስ
አበዳሪ ፣ ክፉ አድራጊ ቢነፍግ ተበ
ዳሪ ፣ እንደተባለው መልካም የሠራ
መልካሙን ዋጋውን ከእግዚአብሔር
ያገኛል ። ክፉ አድራጊም እንዲሁ የክፉ
ሥራ ዋጋውን ያገኛልና ስለዚህ እመቤ
ታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የም
ንወድና የምናከብር ሁሉ የእርሷን መል
ካም ሥራ እየሠራን ለመጠቀም ጭምር
እንጣር ።

ተስፋ ጥሩነህ

# እንክርዳዱ ከወዴት መጣ?

እንክርዳድ ሲባል በመሠረቱ ጸረ አዝር
እት የእህል ጠላት የገበሬዎችን ድካም
ከንቱ የሚያስቀርና ምርቶችን ዝቅ የሚ
ያደርግ አደገኛ ዘር ነው ። እንደሚታወ
ቀው እንክርዳድ ቢበሉትም (ቢመገቡ
ትም) ከጠላ ቢገባም ራስን የሚያዞርና
አእምሮን የሚነሳ የአዝርእት መርዝ
ነው ።

የእንክርዳድ አደገኛነቱ በዚህ ብቻ
ሳይወሰን ከስንዴ ጋር የበቀለም እንደ
ሆነ የስንዴውን ምግብ ወይም ስንዴ
ሊመገበው የሚገባውን ማዕድን እሱ
እየተሻማ ስለ ሚወስድበት ስንዴው
ከዕለት ወደ ዕለት እየቀጨጨና እየመነ
መነ ከጥቅም ውጭ ሲሆን እሱ ግን በጠ
ፋው ስንዴ መካከል እንገቱን ቀና አድ
ርጎ ለምልሞና አፍርቶ ይገኛል ። መሬ
ት ራሱ ሲበላሽ አፈሩ ሲያልቅ እንክር
ዳድ ብቻ ነው የሚያፈራው እንክርዳዱ
ከወዴት መጣ? ስለ ተባለው ጥያቄ ጌታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንክርዳዱን
ምሳሌ አድርጎ ያስተማረውን ትምህርት
ለማስታወስ ያህል ነው ። ገበሬው ለሥ
ራ ትጉና ንቁ እንደመሆኑ መጠን እርሻ
ውን በሚገባ ሲያርስና ሲቆፍር እሾሁን
ሲለቅም ቁጥቋጦውን በእሳት ሲያቃ
ጥል ከባጀ በኋላ ወርኀ ዘር ሲደርስ ማለ
ት እህል የሚዘራበት ጊዜ ሲደርስ ገበሬ
ው ንጹሕ ስንዴ ዘራ አንድ እንክርዳድ
እንዳይገኝበት መላልሶ በማበጠር የደከ
መበትን ስንዴ ከዘራው በኋላ ሲበቅል
እንክርዳድ አብሮ በቅሎ ተገኘ በዚህ
ጊዜ የተዘራው ዘር ንጹሕ ስንዴ ነበር
ይህ እንክርዳድ ከወዴት መጣ ስለተባለ
ነው መልሱ ግን ጠላት የዘራው ተብሎ
ተመልሷል ።

እርግጥም የጠላት ዘር የአዝርእት
መርዝ መሆኑ በግልጥ ይታመናል ይኸ
ውም በድምፅ ማሠራጫዎች እንደ ሰማ
ነው በወሎ ክፍለ ሀገር በአንዳንድ ወረ
ዳዎች መርዝ ሁኖ ሕዝቡን በማሰቃ
የት የሚገኘው እንክርዳድ መሆኑ ለዚ
ሁ በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል ።

ይህ ጠላት የዘራው እንክርዳድ የገበሬ
ሬውን ድካም ከንቱ ከማስቀረቱም ሌላ
በሚመረቱም ምርቶች ላይ ከፍተኛ
ጉዳትና እንዳይሸጡና እንዳይለወጡም
ዋጋ ቢስ አድርጎ እንደሚያስቀራቸው
ተገንዝበናል።ይሁን እንጂ ሌላውን እስ
ቲ ወደ ኅብረተሰባችን ደግሞ መለስ ብ
ለን እንመልከት የኅብረተሰባችን አስተ
ሳሰብ የኅብረተሰባችን አቅዋም እንዴ
ት ነው እንክርዳዳዊ መርዝ ያልተቀላቀ
ለበት ንጹሕ ነውን? በዓለም ላይ አጥፊ
ሁኖ የሚገኘው እንክርዳድ ብቻ አይደ
ለም ሌላም ብዙ እንክርዳድ አለ ።

እንክርዳድ የዘር ጸር የምርት ጠላት
መሆኑ ታምኖበታል በአንጻሩም በሀገራ
ችን አስመሳይ ተራማጆችና እንክርዳድ
መሰሎች እንዳሉ በሥራቸው ተልጋል
ጠዋል ። በቤተ ክርስቲያናችንም በኩል
አንዳንድ እንክርዳዶች ስላሉ ከደረሰ
ባት ከባድ ጉተታ እንዳትሻሻልና በአ
ዲስ መንፈስ እንዳትራመድ የወንጌል
ም ትምህርት በመላ ኢትዮጵያ እንዳይ
ስፋፋና የእግዚአብሔር ቃል ወደ ተጠ
ሙት እንዳይዳረስ የሚጥሩ ከዚህም
ሌላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰግስ
ገው አያስተምሩ ወይም መምህራንን
በየአቅጣጫው አያሰማሩ ቤተ ክርስቲ
ያንን የሚያመነምኑ ብዙ ናቸው ።

እስቲ እውነቱን እንናገር እነ ቅዱስ
ጴጥሮስ እነ ቅዱስ ጳውሎስ በምን ዓይ
ነት ይዞታ ነው ቤተ ክርስቲያንን ይዘ
ዋት የነበሩ። እነዚህ ሰዎች ሌላው ይቅ
ርና የሚወዱት ሰውነታቸው ስለ ቤተ
ክርስቲያን መስዋዕት ይሆኑ እንደ
ነበር ታላቁ የሃይማኖት መጻፋችን ይና
ገራል ።

አዎ የሰው ልጅ ዓቅሙ በሚፈቅድ
ለት መጠን ወጥቶ ወርዶ ለሀገሩ ለወገኑ
ለሃይማኖት ቅዋሚ ቅርስ አትርፎ ለማ
ሳለፍ የማይመኝ አንድም አይገኝም
ነገር ግን ያሰበው ሐሳብ እንዳይሟላ
ምኞቱም ከግቡ እንዳይደርስ ኋላ ኋላ
ውን እየተከተሉ ሐሳቡን የሚያበላሹ
እንክርዳድ መሳዮችና አስመሳይ ተራ
ማጆች እንቅፋት ይሆኑበታል በዚህም
ሁኔታ የታሰበው ሐሳብ ከግቡ ሳይደር
ስ ሕልም ወይም ቅጀት ሁኖ ይቀራል ።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንክርዳ
ድን ምሳሌ አድርጎ ያስተማረው ዋና
ምክንያት ምንድን ነው ብለን ብንጠይ
ቅ እሱ በሚያስተምርበት ወቅት በዘ
ራው ንጹሕ ትምህርት ላይ ለክፋት
ወደ ኋላ የማይሉ አንዳንድ ተንኮለኞች
ነበሩ ጨለማን ተገን በማድረግ በምእ
መናን መካከል እየገቡ ክፋትና ምቀኝ
ነት የሞላበትን እንክርዳድ የሚዘሩ
ብዙ ቢጸ ሐሳውያን በማየቱና በማያገ
ባቸው ነገር እንደ ወተት ዝምብ ጥልቅ
ብለው እየገቡ ምእመናንን ግራ ሲያጋ
ቡ ስለ ነበሩ እነሱንም ምላሽ ለማሳጣት
ና አፋቸውን ለመዝጋት ነበር ። ቀድሞ
በኅብረተሰብ መካከል እየገቡና እንደ
እስስት በተለያየ መልክ እየተለዋወጡ
በሕዝቡ መካከል ብዙ ውጅምብር ይፈ
ጥሩ እንደ ነበረ ዛሬም በቤተ ክርስቲያ
ናችን የዚህ ዓይነት ውጅምብር ሲያንጃ
ብብባት ይታያል ። እንደ እውነቱ ከሆነ
ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር ቤተ ክ
ርስቲያንን ለመምራት የተመደቡ መም
ህራን የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች የሐ
ዋርያትን ፈለግ በመከተል ሐዋርያትን
መስለው በተለይ እነሱ የመንፈሳዊ ጉዳ
ይ መሪዎች እንደ መሆናቸው ምሳሌነ
ነታቸውን ለሁሉ በማሳየት ለተከታዩ
ትውልድ ማስተላለፍ ግዴታ ይኖርባ
ቸዋል ።

ነገር ግን ከዚህ ከተጣለባቸው ከባድ
ኃላፊነት አልፈው ኃላፊነታቸውን ዘን
ግተው በራስ ወዳድነት የግል ጥቅማ
ቸውን የሚያሳድዱ ሁነው ከተገኙ ከስ
ንዴው ጋር የበቀለው እንክርዳድ የስን
ዴውን ምግብ እየወሰደ ስንዴውን አመ
ንምኖት እንደሚቀር ሁሉ በውስጡ
ተሰግስገው ቤተ ክርስቲያንን የሚያመ
ነምኗትንም ሁሉ ራሷ ቤተ ክርስቲያን
ሳትፋረዳቸው እንደማትቀር አያጠራ
ጥርም በዚህ ዓለም ራሳቸው ሳይጠቀሙ
ሌላውንም ሳይጠቅሙ እንክርዳድ ሁ
ነው ከመገኘት በስተቀር ሌላ ውጤት
አይኖራቸውም ቤተ ክርስቲያን ግን
ምን ጊዜም ቤተ ክርስቲያን ናትና ከመ
ሠረቷ አትናወጥም ።

መምህራን ስማቸው የዓለም ብርሃን
ናቸው የዓለም ብርሃንም ከሆኑ እንደ
ስማቸው ብርሃንነታቸው በመላ ዓለም
በሚገኙ ምእመናን ልብ ውስጥ ትምህ
ርታቸው ሠርፆ እንዲገኝ በሚታይና
በሚዳሰስ ሁኔታ ማስተማር ይኖርባቸ
ዋል ።

በሀገር ውስጥ ሀገራቸውን የሚወዱ
ድምበራቸውን በደማቸው የሚያስከብ
ሩ በሃይማኖታቸው የማይጠራጠሩ ሃይ
ማኖተ ጽኑ ልጆችም ሊወለዱ የሚች
ሉት በመንፈሳዊ ትምህርት ከበሰሉ
ቤተ ሰቦች መሆኑን መገንዘብ ያስፈል
ጋል ከዚህ በስተቀር የእግዚአብሔርን
ቃል በሚገባ ካልዘሩና በሕዝቡ ልብ እ
ንዲበቅል ካላደረጉ እንክርዳዱ በስንዴ
ላይ ከሚያመጣው ጉዳት ባላነሰ ከባድ
ጉዳት እንደሚያስከትሉ የማይካድ ነገር
ነው ።

የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና ኃይለ
ኛ ነው በሕያውነቱና በኃይለኛነቱም
ለማዳንም ለማጥፋትም ችሎታ አለው።

እንዲያውም ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎ
ስ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል ኃይ
ል እንዳለው ለዕብራውያን ሰዎች በጻ
ፈው መልእክቱ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል
የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚ
ሠራውም ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይል
ቅ የተሳለ ነው ነፍስንና መንፈስንም
ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረ
ስ ይዋጋል የልብንም ስሜትና ሐሳብ
ይመረምራል ብሏል። ዕብ. 4፥12

ስለዚህ እንክርዳድ ያልተቀላቀለበት
የመዝራት ግዴታ ያለባቸው መምህ
ራን ናቸውና ስለ ቤተ ክርስቲያን መስ
ፋፋት ስለ ወንጌል ትምህርት ላልደረሰ
በት ለማዳረስ ዛሬውኑ መታሰብ አለ
በት ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

# ስሙም ቅዱስ ምሕረቱም ለዘለዓለም ነው

እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ የሆነ
አምላክ ነው ። ለሚፈሩትና ለሚያመል
ኩትም ምሕረቱ ከትውልድ እስከ ትው
ልድ ጸንቶ ይኖራል ። ትዕቢተኞችን
ስለ ልባቸው ክፋት ያዋርዳቸዋል ።
ትሑታንን በኃይል ክንዱ ከፍ ያደርጋ
ቸዋል ። ይህንንም ቃሉ ያረጋግጥል
ናል ። እንዲህ ሲል ፦

ማርያምም እንዲህ አለች ፦ ነፍሴ ጌታ
ታን ታከብረዋለች ፣ መንፈሴም በአም
ላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ፣
የባሪያዪቱን ውርደት ተመልክቶአልና
እነሆም ፣ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ
ብፅዕት ይሉኛል ። ብርቱ የሆነ እርሱ
በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና ፣ ስሙ
ም ቅዱስ ነው ። ምሕረቱም ለሚፈሩት
ከትውልድና እስከትውልድ ይኖራል ።
በክንዱ ኃይል አድርጎአል ፣ ትዕቢተኛ
ችንም በልባቸው አሳብ በትኖአል ፣
ገዢዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል ፣
ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል ፣ የተራ
ቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል ፣ ባለጠጎ
ችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል ። ለአ
ባቶቻችን እንደ ተናገረ ። ለአብርሃምና
ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው
እሥራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል ።

ሉቃ 1 ፥ 46-55

ይህ ተወዳጅ ጥቅስ የተወሰደ ከመጽሐፍ
ቅዱስ ውስጥ ነው ። የቃሉን መንፈ
ሳዊ መልእክት በሚገባ ለመረዳት ቢያ
ንስ ምዕራፉን በሙሉ በእርጋታ ማን
በብ እጅግ አስፈላጊ ነው ስለዚህ መጽ
ሐፍ ቅዱስዎን አውጥተው ይመልከ
ቱት ። ከሌለዎት የክርስትናን እምነት
መሠረታዊ እውቀት የሚገልጽና የሕይ
ወትን መንገድ የሚያመለክት ትክክለ
ኛው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ስለሆነ ገዝ
ተው ዘወትር እንዲያነቡት መንፈሳዊ
ምክራችንን እንለግስዎታለን ። ቅዱ
ሳት መጻሕፍትን በራስዎ ቋንቋ ለማግ
ኘት በሚቀጥለው አድራሻ የኢትዮጵያ
መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን እንዲያነጋ
ግሩ እናሳስባለን ።

የስልክ ቍጥር 12-20-33





www.ethiopianorthodox.org

# "ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት..."

ከመላከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

"ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት" የሚለውን ክፍል ብቻ ብንመለከት የምሳሌው ኃይለ ቃል ሲወረወር በቤቱ ላይ ያረፈ ይመስላል ፣ ውስጠ ምሥጢሩ ግን ቤቱን ሳይሆን ባለቤቱን ለማመልከት የሚሰነዘር ሂስ ነው ። ይህም የኋለኛውን እንጂ የፊተኛውን የድንጋይ ዘመን ሰው የሚመለከት አይደለም ።

ታሪክ እንደሚያስረዳው ጥንታዊው ሰው እንደ ዛሬው ባለቤት አልነበረም ይህም የሆነው እንዲያው በስንፍናና በግድየለሽነት ሳይሆን ቤት ሠርቶ የመኖሩ ዘዴ ያን ጊዜ ገና ያልተከሰተ ጥበብ በመሆኑ ነበር ። ከዚያ ወዲህ ግን የሰው ልጅ ዕውቀትና ጥበብ ቀስ በቀስ እየተሻሻለ በመምጣቱ እንጨት ቆርጦ ሣር አጭዶ የራሱን መጠለያ ቤት በመቀለስ ከፀሐይና ከዝናም ራሱን ለመከላከል ከሚችልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ በዚህ ዓይነቱ ጊዜ አንድ ሰው እንደገና ወደ ኋላ ተመልሶ የጥንቱን ሰው ዓይነት ኑሮ ልኑር ቢል ጊዜው አይፈቅድለትም ፣ መተረቻና መዘባበቻ ይሆናል ።

ሆኖም አሁንም ቢሆን ዓቅም ሳያንሳቸው ዕውቀት ሳያጥራቸው የተራቆተውን ቤታቸውን ሣር አጭደው ማልበስ የሚሳናቸው የጥግንግን ኑሮ ባለቤቶችወይም ክረምት የማይመጣ የሚመስላቸው የበጋ ሰዎች ወይም በሌላ አነጋገር ሰማይን የቤታቸው ጣራ አድርገው በስንፍና ተአምር ከዝናም ለመጠለል የሚሞክሩ የዘመን ብሉይ ሰዎች ያለ ዘመናቸው የሚሞክሩበት ጊዜ መኖሩ አልቀረም ። ነገር ግን የእነዚህ ዓይነቱ ሰዎች ቤት ያው እንደተባለው ግድግዳው ሰንበሌጥ ጣራው ሰማይ እስከ ሆነ ድረስ ዝናም ጠብ ሲል ማረፊያው ወለል ላይ መሆኑ አይቀርም ፣ ነፋስ በነፈሰና ጐርፍ በጐረፈ ጊዜም ከዚህ ዓይነቱ የተፈጥሮ ኃይል ፊት መቆም ስለማይችል እንዲህ ያለው ቤት ሰውም አያከርምም ፣ ራሱም አይከርምም፣ "ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት" የሚያሰኘውም ስለዚህ ነው ።

ይሁንና አሁን ይህን ሁሉ የምንለው እንዲያው ተረት ተርተን ለማለፍ ወይም የገጸ ንባብ ዘይቤ ለማስተማር አይደለም ፣ ፍሬ ነገሩ በዚህ ምሳሌ አንፃር ሌላ መልእክት ለማስተላለፍ ነው ። "ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት" የሚለው አነጋገር በእርግጥ ለብዙ ነገር ምሳሌ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ነው ሆኖም አሁን ለዚህ ጽሑፍ መነሻ አድርገን ያቀረብነው ጥግንግን ቤትን ከደካማ እምነትና ምግባር ጋር በማነጻጸር መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚሰጠውን መልእክት በአጭሩ ለመመልከት ያህል ነው ።

በቅዱስ መጽሐፍ አነጋገር የአንድ ሃይማኖተኛ ሰው እምነትና ምግባር እንደ ቤትና ቤተ ሠሪ ይቆጠራል ፣ ይህንም አባባል ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያረጋግጥ ፣

በእግዚአብሔር ፀጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ አናጢ መሠረትን መሠረትኩ ሌላውም በላይ ላይ ያንጻል ፣ እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንደሚያንጽ ይጠንቀቅ ፤ ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና ፣ መሠረቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅም ቢሆን በብርም በከበረ ደንጋይም ፣ በእንጨትም በሣርም ወይም ቢያንጽ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል ፣ በእሳት እንደሚገለጥ ያቀን ያሳያልና ፣ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል ። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ያገኛል የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ግን ይጐዳበታል ይላል 1 ቆሮ.3፡10-15

በሐዋርያው ዘመን የግሪክ ሥልጣኔ ከተሻለ ደረጃ ላይ የደረሰ ስለ ነበር የጊዜው አናጢዎች የሚሠሩት ዘመናዊ ቤት ባለ እሳተ ከላ መሆን ነበረበት ፣ ይህንም ለማረጋገጥ ቤቱ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ በእሳት ይፈተን ነበር ። ቤቱ በእርግጥ ባለ እሳተ ከላ ከሆነ አናጢው በውሉ መሠረት የሚገባውን ዋጋ ይቀበላል ይህን ፈተና ሊያሟላ ባይችል ግን ኪሣራ በራሱ ይሆናል ። ይህ ዓይነቱ የቤት አሠራር ጥበብ ከጊዜ በኋላ ለሀገራችንም እንግዳ አልነበረም ፣ የመከላከያው ዓይነት ፍጹም ተመሳሳይነት ባይኖረውም እሳተ ከላ ቤት በብዙ ቦታ ነበር አሁንም ይኖራል ።

እንደ ሐዋርያው አመለካከት የእምነትና ምግባር ሁኔታም እንዲሁ ስላልሆነ እያንዳንዱ አማኒ በጥሩ መሠረት ላይ የተጣለ እምነትና በቀና እምነት ላይ የተመሠረተ ምግባር እንዲኖረው ይገደዳል ፣ የዚያ ሰው እምነትና ምግባር ጥሩ መሠረት ያለው መሆኑ ሊታወቅ የሚችለውም ፣

1ኛ/ እምነቱ በእግዚአብሔር ላይ ሲሆን 2ኛ/ ይህ እምነቱ በእሳት በተፈተነ ቁጥር የወርቅነት ጠባዩን በበለጠ ለማንጸባረቅ ሲችል ፣

3ኛ/ እምነት ያለ ሥራ ነፍስ እንደ ሌለው አካል ስለሆነ ማንኛውም የእምነት ሰው "በወሬ ጊዜ ቁልጭ በሥራ ቅቡጭ" የማይል የሥራ ሰውም መሆኑን በተግባር ሲገልጽ ነው ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ዓበይት ነጥቦች በገጽ ሦስትነት ቢኖራቸውም በባሕርይ አንድ ስለሆኑ የሁሉንም አንድነትና ሦስትነት ጠባይ በአጠቃላይ አስተባብሮ መግለጽ ይቻላል ። በዚህ መሠረት "ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት" የሚለውን ቃል መነሻ በማድረግ በዚህ የዝናም ወራት ስለሚገኘው የሃይማኖት ትምህርት ለማውሳት ቢያስፈልግ ዘመነ ክረምት ከሌላው ጊዜ በበለጠ ፈጣሪ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ የሚታወቅበትንና አስደናቂ ሥራውንም በተጨባጭ መንገድ የሚገልጽበት የነገረ መለኮት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ነው።

በዚህ መሠረት አሁን "ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት" በሚለው ትምህርታ

ተከታዩን በ፲፭ ገጽ ይመልከቱ



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት..

ከ፭ኛው ገጽ የዞረ

አድርገውላቸዋል ።

ለቅዱስነታቸው ጉብኝት በወጣው መርሐ ግብር መሠረት በኪቭ ከተማ የሚገኙትን ገዳማት አብያተ ክርስቲያናት የታሪክ ሥፍራዎች ጎብኝተዋል በጀግኖች መታሰቢያ ሐውልት ስር የአበባ ጉንጉን አስቀምጠዋል ፣ የሕሲና ጹሎት አድርሰዋል ።

በ1988 ዓ.ም. የሩሲያ ሕዝብ በቅዱስ ቭላድሚር አማካይነት በጠቅላላው ወጥቶ ስመ ክርስትና ሀብተ ወልድና በተቀበለበት "ኒፕር" በሚባል ባሀር አከል ታላቅ ወንዝ ላይ በዘመናዊ መርከብ ጉዞ አድርገዋል ፣ በዚያም ወቅት የመንግሥት ባለሥልጣናትም ጭምር ስለነበሩ ትምህርታዊና የወዳጅነት ውይይት ተደርጓል። የውይይቱም ኃይል ያመዘነው ኢትዮጵያ በሕብረተሰብአዊነት ለመመራት በታላቅ ርምጃ ላይ ሳለች አንዳንድ የምዕራብ አገር መሪዎች ሃይማኖትህ ሊጠፋ ነው ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ልትመዘበር ነው ፣ እያሉ ሕዝቡ ለነጻነቱ ለአኩልነቱ ለመብቱ ለእናት አገሩ እንዳይታገል በቃላት ሰንሰለት እያሠሩ እንዳያስቸግሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሕዝቧ መቆም እንዳለባት የሚያስገነዝብ ቃል ነበር ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ ካህናት በድሮው ሥርዓት በታላቅ ጭቆናና ርሃብ እየተሰቃዩ የኖሩ እንደመሆናቸው መጠን ለውጡን በደስታ ተቀብለው አብረው እየታገሉ ናቸው ለወደፊቱም ለሕዝባቸው ደኅንነትና ሰላም ከመሥራት የማይቆጠቡ መሆናቸውን አስታውቀዋል። በዚሁ ወቅት 2 የሴቶች ገዳማትን ግብኝተዋል ።

ሬ/ ጉብኝቱ በዑካራይን ውስጥ ወደአለው ልቮቭ ወደተሰኘው ከተማ ቀጠለ ። ወደዚያም የተደረገው ጉዞ በባቡር ነበር ። በዚያም የዚህ ክፍል መንፈሳዊ መሪ ብፁዕ ኒኮላዎስ የልቮቭና ሜትሮፖሊታን ካህናት የመንግሥት ባለሥልጣናትም በታላቅ ክብር ተቀብለዋቸዋል ። በልቮቭና በዙሪያዋ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ቍጥር 963 ሲሆን የካህናቱ ቍጥር ግን 653 ያህል መሆኑ ታውቋል በገጠር የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ደርበው እንደሚያገለግሉ መትሮፖሊት ኒኮላዎስ ለቅዱስነታቸው አስረድተዋል ።

ይህም የሆነው የካህናት ችግር ኖሮ ሳይሆን ብዙ ካህን በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሰብስቦ የኢኮኖሚ ሕፀፅ ከሚያጋጥም ኑሮአቸው የተሻሻለ ሆኖ ጥቂቶቹ ካህናት ብዙውን እንዲያገለግሉ ታስቦ መሆኑ ታውቋል ።

ቅዱስነታቸውና ተከታዮቻቸው የፖቻዮብን የቅድስት ድንግል ማርያም ገዳምና ሌሎቹንም ብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት የታሪክ ሥፍራዎችንና የጀግኖች መቃብሮችንና መታሰቢያዎች ጎብኝተዋል ። በየገዳማቱና በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየተዘዋወሩ ቅዱስነታቸው ጉብኝት በአደረጉበት ወቅት አባቶችና እናቶች ሕፃናት አበባ ይዘው እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በየቤተ ክርስቲያኑ መድረክ ሲደርሱ በሩሲያ ጥንታዊና ባህላዊ መድረክ ሕብስተ አኰቴት ከጨው ጋር ያበረክቱላቸው ነበር ። የኅብስቱና የጨው በረከት የፍቅር መግለጫ መሆኑን አበርካቾቹ በንግግራቸው ገልጸዋል ። በዚህ አኳኋን በልቮብ የሚደረገውን ጉብኝት ፈጽመው በአይሮፕላን ግንቦት 28 ቀን 1970 ዓ.ም. ወደመስኮብ ተመልሰዋል ።



ከላዝቢኒና ከጃፓን ሚትሮፖሊታን ጋር በሞስኮ

## የፖላንድ ጉብኝት

ግንቦት 29 ቀን 1970 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ተከታዮቻቸው በአኤሮፍሎት ተሳፍረው ወደፖላንድ ተጉዘዋል ።

በፖላንድ ርዕሰ ከተማ ዋርሶ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ እንደ ደረሱ አገራቸውንና አብያተ ክርስቲያናቻቸውን እንዲጎበኙላቸው የጋበዟቸው ብፁዕ ባስልዮስ የዋርሶና የመላው ፖላንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መትሮፖሊት፣ ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳትና ካህናት የሃይማኖት ጉዳይና የባህል ምክትል ሚኒስትርና ሌሎችም የመንግሥት ባለሥልጣናት በታላቅ ክብር ተቀብለዋቸዋል ። ወደማረፊያ ቦታቸውም በክብር አድርሰዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በወጣላቸው የጉብኝት መርሐ ግብር መሠረት በዋርሶ ከተማና በሦስት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው በኩራዩብ ከተማ የሚገኙ ጥንታውያን ገዳማት የታሪክ ሥፍራዎችና ሙዚየሞች እንዲሁም በምሥራቃዊ ፖላንድ በኩል የሚገኙትን ጥንታውያንና አዲስ የሚሠሩትን አብያተ ክርስቲያናት ጎብኝተዋል ። በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካ

ተከታዩን በ፲፭ኛው ገጽ ይመልከቱ



በሴሚናሩ በዓል ላይ ንግግሩን ሲያሰሙ



www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንት በትምህርታቸው ሳይሠሩበት እንዳያልፉ ምን መደረግ አለበት ?

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

ቦርንስበሩስ የተባለውና የታወቀው ደራሲ "እን ሥራ ወይም እንለፍ" ሲሉበሰጠው አስተያየት የተመራው ቡቲል ርሆድስም" የሚሠራው ብዙ የተመራው ግን ጥቂት ነው ብሎ ተናግሯል ።

ከሁሉም የሚበልጥ ታላቅ ትምህርት ነው ብለን ልንከተለው የሚገባን የመድኃኒታችን ቃል ደግሞ "መከሩ ብዙ ሲሆን ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው" ይላል ።

እንግዲህ መመሪያዎቹ የሚያሳዩት የሥራን ክቡርነት መሆኑን ልንመገነው ይገባል ወደመጀመሪያው የሥነ ፍጥረት ዓለም የተመለከትን እንደሆነም ለሰው ልጅ "በግምባርህ ወዝ ብላ" ተብሎ የተሰጠው ቃል ጠቅላላው የዓለምን ሕዝብ ፍላጐት በሥራ ላይ ብቻ ይመሠርት ዘንድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው ።

ትርፍ እንዲያስገኝ ገንዘብ የተሰጠው ሠራተኛ የታዘዘውን ባለመፈጸሙ መድኃኒታችን የፈረደበት ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሥነ ሥርዓት ነው ።

የሥራ መነሻና መድረሻ እስከዚህ ድረስ ከሆነ እስኪ እናታችን ወደሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንመልከት ።

በዘመነ ኦሪት የነበሩት ነቢያት ካህናት ፣ ከዚያም ወዲህ በዘመነ ሐዲስ ሐዋርያት ሊቃውንት በየዘመናቸው የሚገባቸውን የሥራ ድርሻ መፈጸማቸውን መጻሕፍት ያረጋግጣሉ ።

ባሁኑ ክፍለ ዘመንስ ለቤተ ክርስቲያናችን በሊቃውንቶቿ ሊቃውንት ተተክተውላታልን? የምእመናንን ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት ለማብዛት በመምህርነት የተሾሙት ሰዎች ችሎታ እስከምን ድረስ ነው? "ያገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" እንደተባለው የአዲሱን ኢትዮጵያዊ ትውልድ ጥያቄ ለማሟላት የሚችሉ መምህራን በብዛት ይገኛሉ? በየቤተ ክርስቲያኑ የሚቀርበው መንፈሳዊ አገልግሎት ምእመናንን ለማስተባበርና ለማቅረብ የሚችል ፣ የቤተ ክርስቲያን ድምጽ በምእመናን ላይ ተሰሚነት እንዲያገኝ የሚያደርግ ነውን? በቀድሞው በአባቶቻችን ባህል ካህን ሲሞት የአባቱን መቋሚያና ጸናጽል ፣ ወታደር ሲሞት የአባቱን ጋሻና ጦር ይዞ የሚተካ ልጅ ይገኝ እንደ ነበረ ይተረካል ፣ ባሁኑ ጊዜስ ይህ ባህል በቤተ ክርስቲያን በኩል ምን ያህል ተጠብቋል?

እንደተባለው በአባቶች እግር ብግብር የሚተካ ልጅ ከተገኘ መልካም ፣ ከሌለስ ለወደፊቱ የቤተ ክርስቲያናችን የሥራ አካሄድ ወዴት ነው?

አባቶቻችን "የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል ብልህ ያለቅሳል" እያሉ በምሳሌ ያስረዱበት የነበረው ቃል ለከንቱ አልነበረም ፣ በቤተ ክርስቲያን በኩል ከሥራ ላይ እንዲውሉ እየተባለ የቀረቡ አሳቦች ፣ የተጠኑም ልዩ ልዩ የሥራ መመሪያዎች አሉ ፣ ሆኖም አሳብ አቅራቢዎቹ ወይም አጥኚዎቹ አሳብንም ሆነ ጥናትን ከማቅረብ የበለጠ የሥራ መብት ስለአልነበራቸው ድካማቸው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀርቷል ፣ ሥራ ተዘዋዋሪ ነው ምናልባት ይኸንን ለመሳሰለው ሁሉ ጊዜ ይገኝለት ይሆን? መልሱ ጊዜው አሁን ነው እንሥራበት ።

ለመሆኑ ሥራው ሁሉ በተገቢው መንገድ የዘመኑን ፍላጐትና አካሔድ ተከትሎ እንዳይሄድ ያደረገው ምክንያት ምን ነበረ?

ለዚሁም በአግጣሚውና በየመልኩ ተንትኖ አጥጋቢ የሆነ መልስ ለመስጠት ይቻል ነበር ። ሆኖም ባጭሩ ለመመለስ ያህል በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ይመደቡ ከነበሩት ሰዎች አንዳንዶች ባለሙያን ሳይሆን ጉሣን በመሰብሰብ የሚያምኑ ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሥራና ሀብት ይልቅ የራሳቸውን ንብረት ክብር ቢዳብር የሚወዱ የሥራ ሰዎች አለመሆናቸው በማንም የማይደፈር ምስጋና መከላከያ የሚሠሩ ፣ እንኳን ደፍሮ የተናገራቸው አሽቅቦ የተመለከታቸው በሕይወት ወይ ሲኦል እንዲወርድና ለምንጊዜም ሕይወታዊ ትንሣኤ እንዳያገኝ የሚያደርጉ ነበሩ ለማለት እንችላለን ።

እንግዲህ ይህ ሁኔታ ከላይ በአርዕስቱ እንደ ተመለከተው ሳንሠራ እንለፍ ቢባል ከሁሉ በላይ የሆነውን የፈጣሪን ትእዛዝ መቃወም ነው ቢባል አይቻልምን? ። ያም ሆነ ይህ የቤተ ክርስቲያንን ሥራ በትክክል ያልተከተሉ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ የራሳቸውን ክብር የፈለጉ ሰዎች በሥራቸው ወድቀው በዚህም ሆነ በማያልፈው ዓለም ፍርዳቸውን በማያወላውል ሁኔታ ይቀበላሉ እንጂ ፣ በአይሁድ ከተሰቀለ በኋላ በምድር ማኅፀን ተቀብሮ ያልቀረው መድኃኒታችን በተቀደሰው ደሙ የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን ወድቃ ወይም ያለ ሥራ ተቀብራ ለምንጊዜም ትቀራለች ማለት ዘበት ነው ።

ከዚህ በላይ ሥራቸው በመጠኑ የተጠቀመባቸውን ሰዎች ሕገ ወጥነትና ራስ ወዳድነት በተመለከትንበት አንጻር ወደቀደሙት አባቶች በጐ ሥራና ጽኑ ሃይማኖት ስንመለከት ግን በሞተ ሥጋ የተሸፈነውን ሰብአዊ ቅርፃቸውን ያልሞተው ታሪካቸው አጉልቶ ያሳየናል ።

ወልጂ እተካለሁ የሚል ተስፋ ያልነበረው ሽማግሌው አብርሃም የፈጣሪውን ትእዛዝ ለመፈጸም ባቁርጥ ሀሊና ይሠዋው ዘንድ እጅግ በሚያሳዝን ልጁ አንገት ላይ ካራውን አሳረፈ ባጭሩም አገላለጽ በእጁ ሳይሆን በሀሊና ልጁን ሠዋው ይህ ነው እውነተኛ ሥራ ፣ እነሆ ከዚህ በላይ የተጻፈውን የደጋግ አባቶች በጐ ተግባር ተከትለው ለመረጃ ሥራቸውን እጅግ በሚያመረቃ ታሪክ ያስጌጡ አሉ ።

ላለፈው ከረምት ቤት አይሠራም እንደሚባለው ሁሉ ያለፈው አልፏልና ለወደፊቱ ለቤተ ክርስቲያናችን ምን ዓይነት ሥራ ይሠራ? ይኸንን ጥያቄ በሙሉ የሚያሟሉ ምሁራን ወይም ሊቃውንት አለማስተማራቸው ቢታወቀንም "የያዙትን ከወረወሩ ፈሪ አይባሉም" ተብሏልና ከሞላ ጐደል ከዚህ ቀጥሎ አሳባችንን እናበርክት ።

ሀ. ምእመናንን በትምህርቱ ለማባዛት ለማቅረብና የአዲሱን ትውልድ ጥያቄ ለማሟላት ፣ ቤተ ክርስቲያንን በችሎታው በትምህርቱ ለማስከበር የቻለ የተማረ ይሾም ።

ለ. ያልተማረ በደጅ ጥናትና በጉሣ በልዩ ልዩ ዘዴ ሳይማር የተሾመ ሹመቱን እያስረከበና ወደፊት ትምህርት ቤት እየገባ ራሱን በትምህርትና በዕውቀት ያሻሽል ። ከዚያም በኋላ በሕዝብ ተመርጦ ወደሹመት መድረክ ይቅረብ ።

ሐ. የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያስናቀ ወይም ያስጠላ የተማሩት ሊቃውንት ቦታ አለማግኘት ነው ለሊቃውንቱ ዕድገት የሚሰጣቸው ሲሆን ግን እነሱ ከደረሱበት እደርሳለሁ የሚለው ሌላው ደግሞ ትምህርቱን በናፍቆት ሊከታተለው ስለሚችል መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶችና ሥርዓተ ትምህርታቸው በትክክል ቢዘጋጅ ሰውን ይስባል ። ምናልባትም ካሁን ቀድሞ ዘመናዊውን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ተብሎ በዩኒቨርስቲና በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት ስላለ ይህ በሚገባ ታይቶ ከሥራ ላይ ቢውል መልካም ነው ።

መ. መተዳደሪያ ከማጣት የተነሣ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ቁጥር በጣም እያነሰ ሔዷል ፣ ስለዚህ ለጊዜው ያሉትን ዐውቆ ወደየ አስፈላጊው ሥራ ለማሠማራት እንዲቻል የብሉያት የሐዲሳት የሊቃውንት ትርጓሜ እንዲሁም የመዝገበ ድጓ የፀዋት ወዜማና የቅኔ የቅዳሴ ዜማ መምህሩን ምን ያህል እንደሆኑ በቅድሚያ በጥንቃቄ ቢመዘገቡ መልካም ነው ።



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት

ከ፱ነኛው ገጽ የዞረ

ከል ለወደፊቱ ሊቀጥል ስለሚገባው የወዳጅነት ግንኙነት በሰፊው ተወያይተዋል ። በፖላንድ የተባበሩት አብያተ ክርስቲያናት ኮሚቴ ታላቅ የሬስፕሽን ግብዣ አድርጎላቸዋል ፣ በኤኩሜኒካል ስብሰባ ላይ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ውይይት ተደርጓል ።

በተለይም የፖላንድ የሃይማኖት ጉዳይ የባህል ምኒስትሩ ከታላላቅ ባለሥልጣኖች ጋር በጽሕፈት ቤታቸው ቅዱስነታቸውንና ተከታዮቻቸውን ተቀብለው አነጋግረዋቸዋል ። ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግንነት ያላቸውን አድናቆት አብስረዋል ። በአሁኑም የለውጥ ጉዞ የፖላንድ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መሆኑ በታላቅ የፍቅር ቃል ገልጸዋል ። የፖላንድና የሶቭየት ኅብረት ክርስቲያኖች ለቅዱስነታቸው ያደረጉት ክርስቲያናዊ አቀባበል ወደር የማይገኝለት እጅግ በጣም ከፍተኛ ነበር ። ቅዱስነታቸው የፖላንድን ጉብኝት ፈጽመው ሰኔ 3 ቀን 1970 ዓ.ም. እንደተመለሱ ብፁዕ ወቅዱስ ፒማን የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ ፓትርያርክ ለቅዱስነታቸው ክብር ታላቅ የምሳ ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣውም ላይ በሶቭየት ኅብረት የምኒስትሮች ምክር ቤት የሃይማኖቶች ጉዳይ ዋና ፕሬዚዳንት በመስኮብ የኢትዮጵያ አምባሳደር ኰሎኔል ፀጋዬ የኤምባሲው ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ተገኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፒመንና ፕሬዚዳንቱ ስለኢትዮጵያና የሶቭዬት ኅብረት ሕዝብ ወዳጅነት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ባልነበረውና ስለሚኖረው ወዳጅነትና ግንኙነት ንግግር አድርገዋል ። ቅዱስነታቸውም መልስ ሰጥተዋል ።

በዚህም ጊዜ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የፖላንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማቴሪያል እርዳታ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ኢትዮጵያንና ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያቀራርብ ጉብኝታቸውን ፈጽመው ሰኔ 7 ቀን 1970 ዓ.ም. ከምሽቱ 5 ሰዓት ሲሆን የነብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው አየር ማረፊያ እንደደረሱ ብፁዕ ወቅዱስ ፒመን የራሽያና የመላው የሶቭዬት ኅብረት ፓትርያርክ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው በክብር ሸኝተዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸውም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ሰኔ 8 ቀን 1970 ዓ.ም. ከቀኑ ሦስት ሰዓት ሲሆን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አኤሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቤ/ክህነት ሥራ አስኪያጅ ቀሲስ ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤልና የቤተ ክህነት ሹማምንት የደብር አለቆችና የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በመጋቤ ካህናት ብርሃኑ መኰንን አስተናባሪነት ከፍ ያለና የደመቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው በአኤሮፕላን ማረፊያ አዳራሽ ተገኝተው ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል፣ ከዚያም በክብር ተከታዮቻቸው ታጅበው ወደ መንበረ ፓትርያርክ ቅ/ቅዱሳን ማርያም በማምራት ከተጓዙ በኋላ ወደቤተ ክርስቲያኑ ገብተው አጭር የሕሊና ጸሎት አድርሰዋል ቀጥሎ ወደ መንበረ ፓትርያርካቸው አምርተው ከተመደበላቸው ሥፍራ እንደቆሙ መዘምራት በዝማሬና በሽብሸባ ተቀብለዋቸዋል ። አንዳንድ ሊቃውንት የክብር ቅኔዎች ካበረከቱላቸው በኋላ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጐጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የልማት ኮሚሽንና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ስለጉብኝቱ አጭር ንግግር አድርገው እንዳበቁ ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው የአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኖአል ።

ከቅዱስነታቸው ጋር የክብር ተከታዮች ሆነው የሄዱት 1ኛ/ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጐጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የውጭ ጉዳይና የልማት ኮሚሽን ኃላፊ 2ኛ/ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የከፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ 3ኛ/ ቀሲስ ሰሎሞን ገ/ሥላሴ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ 4ኛ/ ዶክተር አባ ሀብተ ሥላሴ ተስፋ በውጭ ጉዳይ ክፍል ናቸው ።

# "ክረምት ...

ከ፰ኛው ገጽ የዞረ

ዊ ምሳሌ ላይ የጀመርነውን ትምህርታዊ ጎተታ አስቀድሞ በተጠቀሰው ሐዋርያዊ መልእክት ለማጠቃለል ለሰው ልጅ ዋናው መኖሪያና ማደሪያ ቤቱ ሥራው ነው ። ለዚህም ቤት መሠረቱ እምነት ነው የሚሠራ በእምነት ይሠራል ፣ በሥራም ይኖራል ራሱንም ያሳድራል ያስተዳድራል ስለዚህ ቤቱን በዚህ ዓይነት መሠረት ላይ የገነባ ቤተ -ሠሪ እርሱ በእርግጥ ባለቤት ነው ። "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ቤትን የሚሠሩ ሰዎች በከንቱ ይደከማሉ " ተብሎ በቃለ መጽሐፍ እንደተነገረው ቤቱን ከእግዚአብሔር የሚሠራ ብልህ እናጢ ነውና ።



## ሊቃውንት በትምህርታቸው ........

ሠ. የትርጓሜ መጻሕፍት መዲናዎችና ምንጮች የሆኑትን ጐንደር ጐጃም የዜማ ቦታ የሆነው ጐንደር በተለይ የድጓ ማስመስከሪያው ቤተ ልሔም የቅኔው ቦታዎች ዋድላ ዋሸራ የመሳሰሉት የቅዳሴ ዜማ ቦታዎች ደብረ ዐባይ ስለልኩላ እነዚህ ሁሉ በሚገባ እንዲጠነክሩና እንዳይቋረጡ ተገቢ የሆነ እንክብካቤና መተዳደሪያ ቢደረግላቸውና የሥራ መመሪያ ቢሰጣቸው ሥራው ያምራል ።

ረ. በቀድሞው ዘመን አንብበው ለሚተረጉሙ ፣ መርተው ለሚቀኙ ተጠይቀው ለሚያስረዱና ለሚያስተምሩ ሊቃውንት ይሰጥ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ሹመት አብዛኛው ላልተማሩ ሁኗል ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሹመት ከሥልጣነ ክህነትና ከትምህርት ሊሆን ይገባል ።

ሰ. ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን ፣ ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን ጋር በይበልጥ የሚገናኙበት የሰበካ ጉባዔ ስለ ተቋቋመ ሥራው በሁሉም ዘንድ መሠራትና መጠበቅ አለበት ።

ቀ. የወንጌል ትምህርት ከሳይንስ ጋር እንዳይጋጭ ሆኖ ለዘመኑ ትውልድ ተስማሚ የሆነ በዕድሜ የበሰሉትን አረጋውያን የማያስቀጣ የሆነ ቢሰጥ ውጤቱ ያምራል ይኸውም ትምህርትን ባህልን ሃይማኖትን ታሪክን በጐ ምግባርን የመሳሰለውንም ሁሉ የሚገልጽ መሆን አለበት ።

ሸ. የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት በጠቅላላው ከአንድ ግምጃ ቤት ገቢ እየሆነ ካለው ለሌለው በማካፈል ቢዳረስ የቤተ ክርስቲያን ሥራ በትክክል ሊሠራ ይችላል ።

ቀ. አስተዳደሩ በአስተዳደር ዐዋቂዎች መንፈሳዊው ሥራና ትምህርት በተማሩት ሊቃውንትና ምሑራን ይካሔድ ማለት ሁሉም በየችሎታውና በየዕውቀቱ ቢሰለፍ የሥራ ፍሬ ሊሰጥ ይችላል ።

በ. ለዚህ ሁሉ ዋናው መመሪያው ወይም መክፈቻው ደምብ ስለሆነ ለአስተዳደሩ ለትምህርቱ ለሹመቱም ሆነ ለሽረቱ ደምብ ቢወጣ አሠራሩ ትክክለኛ ሊሆን ይችላል ።

ተ. በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል እንደተባለው ለስብከት ለትምህርት ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚጠቅሙ መጻሕፍት በሊቃውንት እየታረሙና እየተዘጋጁ ቢታተሙ መልካም ነው ።

ቸ. በየትምህርት ቤቱ የሚማሩ የኢትዮጵያ ምእመናንን ልጆች የባቶቻቸውን ሃይማኖት ባህል ሥነ ምግባር እንዲከተሉ ልዩ ልዩ ፕሮግራም እየተዘጋጀ ትምህርት ቢሰጣቸው መልካም ነው ። ተከታዩን በ፲፩ኛው ገጽ ይመልከቱ

www.ethiopianorthodox.org

# ሥራና እምነት በሴቶች ሕይወት

ሐዋርያው ያዕቆብ በመልዕክቱ ሥራ ያለዕምነት ዕምነትም ያለ ሥራ የሞተ እንደሆነ በግልፅ ጽፎ እናገኘዋለን ።

እምነትና ሥራ በአንድነት ተዋህዶ ሲሰራበት ምን ያህል አስደሳችና የኑሮን ሁኔታዎች ሁሉ አሟልቶ ያያዘ መሆኑን በሴቶች ሕይወት በበለጠ ተተርጉሞ ሲሰራበት እናያለን።ብዙ ሥራ ስለ አለብኝ የአምልኮት ጊዜ የለኝም ወይንም ሠራተኛ ከሆንኩ ዕምነት አይጠቅመኝም ሳይሉ ያላቸውን ዕምነት ከሥራቸው ጋር አዋህደው ሲገልፁት ማየት እጅግ ያስደስታል ።

እነዚህን ዋና የሆኑ ሁለት ነገሮች በሕይወታችን ለመተርጐም ለጊዜው ከባድ ቢመስለንም ያለዕምነት ሥነ ሥርዓት ያለው የኑሮ አመራር ያለ ሥራ ደግሞ ምግብና ልብስ ሊኖረን ስለማይችል ተግተን ለመፈጸም ብንሞክር የተቃና አካሄድን ስለሚሰጠን ሰዎች እምነትንና ሥራን አዋህደው ቢይዙ እውነተኛውን የኑሮ ጣዕም ለማግኘት ከሁለቱ የበለጡ ነገሮች የሉም ።

ስለዚህም ሴቶች በሥራ ቤታቸውን ለመገንባትና ቤተሰቦቻቸውን ለመጠበቅ በዕምነት እየተመሩ ትክክለኛውን የኑሮ ሂደት ለመያዝ በአንድነት ሲያካሂዱት ማየት ለአርቆ አስተዋዮች የተሰወረ አይደለም ። ሥራን ከዕምነት ጋር አቀነባብሮ መያዝ የኑሮ ፈሊጥን ማግኛና ትልቅ ሙያም ጭምር ነው ።

ለምሳሌ ይህ የፍልሰታ ጾም ክርስቲያኖች በሙሉ ሕጻናት እንኳ ሳይቀሩ ያላቸውን ዕምነት በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው በሚደረገው ጾምና ፀሎት የሚገልፁበት ነው በሌላ በኩልም ደግሞ የሥራ ጊዜ ነው ሁለት ሥራዎችን በአንድነት ማካሄድ እንግዲህ እንዴት ከባድ እንደሆነ እናስተውል ቢሆንም በሴቶች ምንም የሥራ ብዛቶች ቢሰበሰቡም ካላቸው እምነት ፈቀቅ ለማለት በጊዜ እጥረት ወይንም በሌሎች ነገሮች ሳያሳብቡ በቤት ያላቸውን ስፍር ቍጥር የሌለው ሥራና የወጪውም ሳይቀር በመጐልጐል በማረም በመኰትኰት ነው ። በቤት ውስጥም ቤተሰቦቻቸውን በመመገብና የሚያስፈልጋቸውንም ሁሉ በማድረግ በጠቅላላው የቤተሰባቸውን መሪነትና ሐላፊነት ሳይዘነፉ ጠብቀው በእምነት በኩል ያለውንም ደግሞ ለማካሄድ በጥሩ ሁኔታ የተከተተ ልብሳቸውን ለብሰው ባዶ እጃቸውን ሳይሄዱ ደግሞ ጥሬ ካላቸው ወይም ከንጀራ ቆርሰው ለሌሎች የሚያጐርሱትን ይዘው ወደቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ ። ይኸ ዕምነታቸውን ከመጠበቅ ጋር የሚያደርጉት በጐ ሥራቸው ሲሆን በሌላ በኩልም ያላቸው እምነት ሁሉ በሥራ ሲተረጐም የቤተሰቦቻቸው የዕምነት አስተማሪ ፣ ባገኙት ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ መልካም ያልሆኑትን ሲቃወሙ ይኸን እግዚአብሔር አይወድም የሚሉ ፣ የቤተሰቦቻቸው ታማኝና የቅርብ ተጠሪዎች ሴቶች ናቸው ። ቤተ ሰብን ማስተማር ሀገርን ማስተማር ነው እንዲሉ በተግባር በሚያሳዩት ሥራዎች ሁሉ ዕምነታቸውንና ሥራቸውን በግልፅ የሚያሳዩ በጧት በማታ የፈጣሪአቸውን ስም ጠሪዎች ለሚጀምሩት ሥራ ባላቸው እምነት ስም እግዚአብሔርን የሚጠሩ ዕምነታቸው ሥራቸውን ሥራቸው ዕምነታቸውን ያላጓደለባቸው ፍጹም ክርስቲያናዊ አኗኗርን በሕይወታቸው በመተርጐም ከቤተሰብ እስከ አካባቢአቸው በአንድነት የሚኖሩ የቤት እመቤቶች ሥራቸውን ካላቸው ዕምነት ጋር አስተካክለው የሚኖሩ የቤት ሐላፊዎች ሴቶች ናቸው ብንል እውነቱን ሐሰት ማድረግ አንችልም ።

በከተማችንም ብንሄድ በሌሎች የሥራ መስኰች እንኳ ቢሰማሩም በሚቻለው መጠን ሁሉ ዕምነታቸውን ከሥራቸው ለመለያየት የማይፈቅዱ ብዙ ሴቶች አሉን ። በዚህች በፍልሰታ ወቅት እንኳ ልብ ብለን ብንመለከት ሕጻናት እንኳ ሳይቀሩ በቤት የሚሰጣቸውን የየአቅማቸውን ሥራ ፈጽመው ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ያላቸውን ፍላጐት እንመልከት ይኸን ሁሉ ስናጤነው ዕምነት በሴቶች ሕይወት የበለጠ ተተርጉሞና በሥራ ላይ ውሎ እንመለከተዋለን ። እንደ ሴቶች እምነትና ሥራ በአንድነት አሟልቶና አገናዝቦ የያዘ ደረጃ ይሆን ? ምክንያቱም ያሉባቸው ብዙ ሥራዎችና ከቤተ ሰብ እስከ አካባቢ ያለው ኃላፊነት ከእምነታቸው ሊለያቸው ወይም ሥራቸው እንዲበልጥ ባቸው አላደረጋቸውም ። ነገር ግን ባላቸው የሥራ ብዛት ላይ ጨምረው እምነትን ከሥራ ጋር ማጣመራቸው እንደ ዘበት ታይቶ የሚቀር ወይም በአድናቆት ብቻ የሚታለፍ መሆን የለበትም ። ስለዚህ ከነገሮች ሁሉ መጣርና ሕይወታችንን ከመልካም ነገር እያይዘን መምራት ስለአለብን ከሴቶች ሕይወት መውሰድ ያለብንን ብዙ ነገሮች እንደ ዘበት እየተመለከትን ልናልፈው አይገባም ። እንደ ሐዋርያው አባባልም ዕምነታችንና ሥራችንንም በአንድነት እንዲሆንልን ብናጠነክረው መልካሙን ሕይወት መረጥን ማለት ነው ። ሕይወት የቀልድ ዘመቻ አይደለምና ከዕምነት ነጥለን ልናኖረው ብንሞክር ብዙ ጉድለቶችና በሥራችንም ብቻ አሟልትን ልንዘልቃቸው የማንችለው ችግሮች ሊገጥሙን ይችላሉ ።

ይኸ ከሆነም ዕምነታችንና ሥራችንን አቀነባብረን ከመያዝ በስተቀር የተሻለ ምርጫ የለም ዕምነታችን የሚያስተምረን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የተቃና ኑሮን የምንኖርበት ሲሆን በሥራችን ደግሞ ልንኖርበት የምንችልበትን ነገር ለማዘጋጀት ይሆናል ። እንደገናም በዕምነታችን ለእግዚአብሔር በ

ተከታዩን በ፳ኛው ይመልከቱ

# ምሥራቅ ጀርመን ፡ የ1970 ዓ.ም. የሥነ ስቅለት ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ በቴሌቪዥን ተላለፈ ።

የምሥራቅ በርሊኑ የፕሮቴስታንት ጳጳስ አልበርት ሰሆንከር ለ8 ደቂቃ ያህል ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ስቅለት ትምህርት በቴሌቪዥን ሰጥተዋል ።

ትምህርቱ ከተላለፈ በኋላ በምሥራቅ ዲሞክራቲክ ጀርመን መሪ አሪክክ ነከርና በሀገሪቱ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሊቀ መንበር በተደረገው ውይይት የአብያተ ክርስቲያናቱ አበይት በዓላትና ስለ አብያተ ክርስቲያናት የሥራ እንቅስቃሴ በየወሩ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ እንዲተላለፍ ተስማምተዋል ሲል የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛና የማሰራጫ ዘዴዎች ማኅበር በግንቦት ወር ጋዜጣው ገልጿል ።

## ታላላቅ መንፈሳዊያን ስብሰባዎች

በአንድ ሣምንት ውስጥ ሁለት አበይት መንፈሳዊያን ስብሰባዎች በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ውስጥ ሲካሄዱ በስብሰባው ላይ ብዛታቸው ወደ 75.000 የሚደርስ ምዕመናን ተካፋይ መሆናቸው ታወቀ ።

ስለእነዚሁ ስብሰባዎች የተገኘው ዜና እንደ ገለጠው ከሆነ ፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ድርጅት በመወከል በስብሰባዎቹ ላይ የተገኙት የድርጅቱ ረዳት ዋና ፀሐፊ ቀሲስ ክንራድ ሬይሰር በሰጡት መግለጫ "ስብሰባዎቹ ለክርስቲያኖች የመልካም ብርታት ምልክቶች ከመሆናቸውም በላይ ከዚያ አገር ያሉ"አብያተ ክርስቲያናት ሊፈፅሙት የሚገባውን ተግባር መስከሯል ብለዋል በዚሁ ላይ ካህኑ ሲናገሩ "በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የሚገኙ ክርስቲያኖች እርስበርስ የሚካፈሉትና እንዲሁም ለክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ከዚያም ለአብያተ ክርስቲያናት አንድነት የሚያጻርሱት መልእክት አግኝተዋል" ሲሉ አስረዱ በዚሁ ላይ ጨምረው ቀሲስ ክንራድ ሬይሰር ሲያስረዱ፡-"ስለ አብያተ ክርስቲያናት ህብረትና ስለዓለም አብያተ ክርስቲያናት በኤርፋርትና በሊይፐዚግ ከተማ ተነስቶ በተመሳሳይ መንገድ ምዕመናኑ ስለተነጋገረበት ተገርሚአለሁ" ብለዋል ።

ስምንቱ ትላልቅ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን የመሳሰሉ አበይት ስብሰባዎች ሲያዘጋጁ ብዙ ዓመታት ማለፋቸው ተጠቅሷል።ዜናው ቀጥሎ ሲያስረዳ፣በሐይ ፕዚግ ከተማ የተካሄደው ይህ ስብሰባ ሲደመደም ብዛቱ 50.000 የሚደርስ ሕዝብ ተገኝቷል ። ብሏል ፣ ይህ በአገሪቱ በ25 ዓመት ውስጥ ከተደረጉ ስብሰባዎች እጅግ በጣም የላቀ መሆኑን በመጥቀስ ፣ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምዕመናን መሀል ግማሾቹ እድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች የሆን ወጣቶች ነበሩ ብሏል ። በዚሁ ስብሰባ ወቅት ብዛታቸው ወደ 4.200 የሚሆን ምዕመናን በሁለት መቶ ወርክሾፖች ወይም መርሐ ግብሮች በመክፈል "መኖር ማለት ዓላማ ሲኖር ነው' በሚል ርዕስ ላይ ተነጋግረዋል ።

በዚሁ ስብሰባ ጊዜ በአገሪቱ ርዕስ ብሔርና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሀልም ውይይት ተደርጉአል ።

## የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና የጦር መሣሪያ ቅነሣ

በኒውዮርክ ከተማ በሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በመካሄድ ላይ ባለው የጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ንግግር እንዲያደርጉ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ፀሐፊ ዶክተር ፊልፕ ፐተር ጥሪ መቀበላቸው ተነገረ ።

ይህንኑ ጥሪ አስመልክቶ ኤኩሙኒካል ፕሬስ የተባለው መጽሔት ሲያብራራ ፣ ዶክተር ፒተር የተጠሩት ከመንግሥታዊ አካል ያልሆኑ የግል ድርጅቶች የሚወክሉ እውቅ የሆኑ ሰዎች በጦር መሣሪያ ክምችት ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲያቀርቡ ለተመደበው ዕለት ነው ብሏል ።

ዶክተር ፊልፕ ፐተር በንግግራቸው ላይ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በመሣሪያ ክምችትና ቅነሳውም ላይ ያለውን አሳተያየት የሚያብራሩ ሲሆን ፣ ድርጅቱ ለረጅም ጊዜ የጦር መሣሪያዎች እሽቅድምድም በሚመለከተው ረገድ አስተያየቱን ሲሰነዝር እንደነበረ ያቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በ1967 ዓ.ም. ናይሮቢ ላይ ተሰብስቦ በጦር መሣሪያዎች ቅነሳ አስፈላጊነት ከተወያየበት ጊዜ ጀምሮ በድርጅቱ ሸንጐዎች ውስጥ ይህ ጉዳይ ተቀዳሚነት አግኝቶ ቆይቷል ።

ይህንኑ የጦር መሣሪያዎችን እሽቅድምድምና ክምችትን በሚመለከቱት ጉዳዮች ላይ የድርጅቱ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ክፍል ሁለት የተለዩ ጉባዔዎችን በሁለት ዓመታት ውስጥ ማድረጉ ታውቋል ። ከዚህም በስተቀር ገና በ1953 ዓ.ም. ሳይቀር በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት የዓለም አቀፍ ጉዳዮች ክፍል የጦር መሣሪያዎች እሽቅድምድም ባጭሩ እንዲገታ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ ጉባዔ እንዲደርግ ማሳሰቢያ አሳልፎ እንደነበር ይኸው የድርጅቱ መጽሔት ጠቁሟል ።





www.ethiopianorthodox.org

# የሠራተኞች ኃይል እንዳይከፋፈል

ሠራተኞች ስንል ለሰው ልጆች ስለሰው ልጆች መልካም አገልግሎት የሚሠጡትን ነው ሥራም ሲባል ለዓለም ኅብረተሰብ የሚሰጥ መልካም የበረከት ፍሬ ነው ። በዚህ አንፃር ስለቤተ ክርስቲያንና ስለምእመናን ስለጠቅላላውም የሰው ልጆች ያለንን ፍቅርና ስሜት ስናስታውስ በተለይ በቀድሞ ጊዜ በቤተክርስቲያንና በምእመናን ላይ የደረሰውን የሠራተኞች ኃይል መከፋፈል የጠቅላላውንም ሊቃውንት የኑሮ ሁኔታና የአሠሪዎችም በሥራ አለመተባበር ከሁሉ አስቀድሞ መረዳት እንዳለብን ይሰማናል ።

አንድነት ከተከፋፈለና የአሠሪዎችም ሆነ የሠራተኞች የሥራ ኃይል ካልተባበረ እንደኩሬ ውሃ ካለበት ቁሞ ከመቅረት በቀር እየመነጨ ወደ ሌላ መፍሰስ አይችልምና የአንድነትም ሆነ የልማት ሥራ አይንቀሳቀስም ።

ለምሳሌም በአራተኛው ክፍለ ዘመን በመጀመሪያውና በመጨረሻው ግድም አንዳንድ ሊቃውንት ስለነገረ መለኮት እየተነታረኩ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው ሥራ መወዘፉ አልበቃ ብሎ በዘመኑ የነበሩት ምእመናን እነሱን በማስታረቅ የሥራ ጊዜያቸውን በከንቱ እንጓሳለፉትና ሰላም አጥተው ቤተ ክርስቲያንንም ሰላም እንደነሷት ታሪክ ያወጋናል ።

ሆኖም ወንጌልን ለማስተማር ቤተ ክርስቲያኗን ለማስፋፋት የሠራተኞችን ኃይል ማስተባበር ይጠይቃል እንጂ ክርክርን አይደለም ፣ ክርክር ግን ተስማምቶ መሥራትንና መግባባትን እያራቀ መለያየትንና መከፋፈልን ስለሚያመጣ የሥራ ኃይልን ያዳክማል ይህም ለውጭ ጠላት መመቸትንና በራስም ላይ ችግርን ከማስከተል በቀር ሌላ ትርፍ የለውም የአንድነት መሠረቱ እርስ በርስ መለያየት ሳይሆን የሥራ ኃይልን አስተባብሮ ጥቅምን በሚሰጥና እድገትን በሚያስገኝ ሥራ ላይ ማዋል ነው ።

ያለፈው ጊዜ በቤተ ክርስቲያን በኩል በዚሁ ረገድ ያለ ሲሆን በዘመናችን ያለው የቤተ ክርስቲያን ይዞታ እንዴት ነው የሚል ጥያቄ ይገጥመን ይሆናል ። የነገረ መለኮት ክርክር ባይኖርም የደብሩ አንዳንድ አለቆችና ካህናት እንዲሁም አንዳንድ አሠሪዎችና ሠራተኞች በየካቲት ወር 66 ዓ.ም. የመጣውን ለውጥ ተከትለው ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ማኅበር በማቋቋም በእኩልነት እየሠሩ በስምምነት መኖራቸውን ትተው እርስ በእርሳቸው እየተጨቃጨቁ የሰላምና የፍቅር አደባባይ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን የጭቅጭቅና የጥል መድረክ ስላደረጓት ያሳዝናል ይኸውም የሚጨቃጨቁበት ዋና ምክንያት ወንጌል እንዲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን እድገት እንድታገኝ ፣ ምእመናን እንዲበዙ ሳይሆን ደመወዙ ከእገሌ ጋር ይስተካከል ፣ በእውቀቱ ልክ አላገኘሁም ፣ እኔ ከማን አንሳለሁ በሚል የግል ጥቅም ነው ።

የቀድሞቹ አንዳንድ ጊዜ ቢነታረኩም ስለነገረ መለኮት እንጅ የግል ጥቅምን በማሳደድ አልነበረም የአሁኖቹ ግን እርስ በእርሳቸው የሚጣሉት ለግል ጥቅም በመሆኑ ነገሩ ተዛወረና ምእመናኑ አስታራቂ ካህናቱ ታራቂ ሆነው ይታያሉ ፣ ይህም አልበቃ ብሎ እየተካሰሱና እየተከሰሱ በየፍርድ ቤቱ ስለሚታዩ ለፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ችግር ፈጥረው በታል ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይጨቃጨቁና ይሟገቱ ለነበሩ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ሲል ጽፎአል ። "በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን ? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል ይህ ሊደረግ ይገባልን ?

ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ ያውም ወንድሞቻችሁን' ብሎአል 1ኛ ቆሮንቶስ ም 6 ቁ.5-8

እንዳለውም የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሰላም ልኡካን ስለሆኑ ሊጣሉ አይገባቸውም ድንገት እንኳን ሲጣሉ በሽማግሌ መታረቅ እንጂ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ አይገባም ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጡ ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ በሚለው የጥንት ዘይቤ ካህናት አልጫን የሚያጣፍጡ ጨው ናቸው እንጂ ሌላውን አልጫ የሚያደርጉ አይደሉም በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ የማይሰወሩ ናቸው እንጂ ከእንቅብ በታች የተቀመጠ መብራት አይደሉም ።

እርግጥም ብርሃቸው በሰው ፊት የማይበራ ከሆነ ግን የሚያገለግሏት ቤተ ክርስቲያን ትናንት የነበረውን ይዞቷን ሳትለቅ ጨምዳ ይዛ እንቅስቃሴንና አዲስ የሥራ ለውጥን አታሳይም እንዲህ ያለውን ሁኔታ በቤተ ክርስቲያኑ ያሉ አሠሪዎችና ሠራተኞች የማይተው ከሆነ የሥጋ ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ችግር የሚያመጣ መሆኑን ቀደም ብሎ የተገነዘበ አንድ የሥራ ሐዋርያ ያልሠራ አይብላ ሲል አስተምሮ ነበር ።

እንዳለውም ጊዜአችን የሥራ ጊዜ በመሆኑ ቁጭ ብሎ እየተከራከሩ የሚበላበት ትናንት ከሊቃውንቱ ጋር አብሮ ሔዷል በምዕዋት በአትርሱኝ የሚኖር በትም ዘመን አልፎአል ወደ ላይም ቢያንጋጥጡት ከሰማይ መና አይወርድም ያለፈው ነገር ሁሉ ተመልሶ ስለማይመጣ ትናንት ዛሬ አይደለም ትላንት ስለሞተ በዛሬ መኖር እንጂ በትናንት መኖር አይገኝም ነገም ገና ያልተወለደ ፅንስ በመሆኑ ትርጉሙ አይታወቅም ።

ስለዚህም የናዝሬቱ ኢየሱስ "አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ ለቀኑም ክፋቱ ይበቃዋል" ሲል አስተምሮአል ።

ይህም ማለት ነገ ለራሱ ከባድ የሥራ ቀንበር ስላለውና አዲስም ሥራ ይዞ ስለ

ተከታዩን በ፲፭ኛው ገጽ ይመልከቱ



# ቤተ ክርስቲያንና ውለታዋ

ቤተ ክርስቲያን ውለታዋ ምንድነው ? ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባልዋት ፊደላት ያሉዋትን ሰዎች አስተምራ ራሳቸውን ስታስችል ባገኙት እውቀት አምላካቸውን እንዲያውቁ አስችላቸዋለች ፣ ይህን ከማድረጉዋም ሌላ ባሉዋት ፊደላት ሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበባትን ለሰዎች ሁሉ በእኩልነት በማስተማርዋ የማይረሳ ውለታን አበርክታለችና ።

ቤተ ክርስቲያን ቀድሞም ሆነ ዛሬ በከፍተኛ ቦታዎች ላይ በተለያዩ ጸድቃንና ሰማዕታት ቅዱሳን መላእክት ስም ቤተ መቅደሳችን ስታሠራ በዚያው ሳቢያ በደን ልማት በኩል ዛሬ እንደሚደረገው ከፍተኛ ጥረት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ግን ቀደም በማለት አጸዶችን በማስተከል ለቦታው ድምቀትን ንጹሕ አየርን እንዲሰጡ ዝናመ ምሕረትን እንዲያስጥሉ ሆነው ቆይተዋል እንዲሁም ዛፎች በልምላሜአቸው ተመልካችን በሩቅ ሲስቡ እንደኖሩ በማንኛችንም ዘንድ የታወቀ ነው ።

የቤተ ክርስቲያንን ውለታ ቀረብ ብሎ ለቀመሰውና ለተመለከተው በቀላሉ የሚዘረዘር አይደለም በጸሎትዋና በምልጃዋ ከፈጣሪ ዘንድ ከምታሰጠው በረከት ሌላ በቅዱሳኖችዋ ስም የሚጠሩ በየቦታው በሚፈልቁ ጠበሎችዋ ረድኤት እግዚአብሔር በተመላባቸው ቅዱሳት መካናትዋ ሣይቀር አምነው የቀረቡዋትን ከማይታይና ከሚታይ ደዌ እየፈወሰች ሕዝቡን ከከባድ ደዌ አድናለች ። ለምሳሌም ያህል ጥቂቶቹን ብንጠቅስ የሐመረ ኖህ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ጠበል ፣ የሚጣቅ አማኑኤል ጠበል ፣ ለብቃ ኢየሱስ ደብረ ሊባኖስ ፣ በወሊሶ የመምሕር ወ/ትንሣኤን ጉርደማ እግዚአብሔር አብን ጠበል የመሳሰሉትን መጥቀስ ያስፈልጋል በዚህ መልክ የቤተ ክርስቲያን ውለታ እጅግ የማይረሳ መሆኑን ልንገልጽ እንወዳለን ።

ቤተ ክርስቲያን በጥንታዊ ታሪኳና መንፈሳዊ ቅርሷ እጅግ የታወቀችና የተወደደችም ሆና ኖራለች ፣ ባላትም ቅርሳ ቅርስ ከአገር ቀርቶ ከውጭ አገር ጐብኛች በርካታ ገንዘቦችን አስገኝታለች በቅርሳቅርስ ከታወቁት አብያተ ክርስቲያናትም ለመጥቀስ ቢያስፈልግም ቅዱስ ላሊበላ ፣ አክሱም ጽዮን ፣ ግሸን ማርያም ፣ ጣና ቂርቆስ ፣ ደብረ ቢዘን እና ደብረ ሊባኖስን የመሳሰሉ እናገኛለን በቦታ(መንገድ)አለመመቸት እጅግ የታወቁ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት እንዳሉ ግልጽ ነው ።

በሌላ በኩል ጸሎት ሐይል መሆኑን በማስተማር በጸሎት ኃይል ብዙ ተአምራትን አሳይታለች ታሳያለችም ለምሳሌ በሚደርስብን ቀላልና ከባድ ችግር ከዚችው ቤተ ክርስቲያን ተጠግተን በግልና በማኅበር ጸሎት ተማጽነን ከፈጣሪያችን ተማልዳ በማማለድ ከከፍተኛ ችግር ያዳነችን ለመሆንዋ ሥውር አይሆንም ስለዚህ ይህን ውለታዋን በማሰብ ከአባቶች የተረከብናት (የምንረከባት) ወጣቶች ሁሉ በአለን ትክሻ ኃይል እንከባከባት በማለት መንፈሳዊ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።

የኢትዮጵያ ኦ. .ተ. ቤ. ክ. የወጣቶች መ. ማ. አጠቃላይ መምሪያ

## ሊቃውንት-.........

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞረ

ኀ. የሴቶች በመንፈሳዊ ተግባር ተካፋይነት በብሉይም ሆነ በሐዲስ ያለ ነው ። ስለዚህ ሴቶችም በቤተ ክርስቲያን በኩል ያላቸውን የሥራ ድርሻ ዐውቀው እንዲሠሩ ቢደረግ ሕብረቱ ሊጠነክር ይችላል ።

ነ. በገዳማትም ሆነ በቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተግባረዕድ እንዲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው መድከም ይኖርበታል ። "ወደኔ የመጣውን ሁሉ ወደ ውጭ አላስወጣውም" ባለው የመድኃኒታችን መመሪያ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ትንሽ ትልቅ ደሀ ጌታ ዐዋቂ ሳትለይ የማኅበራዊ ኑሮ መመሥረቻ ሆና ትኖራለች ፤ አሁንም ይህን የኖረውንና ጊዜ የሚፈቅደውን ባህሏን በዓዋቂዎች እያስጠናች በሥራ ላይ ልታውለው ይገባል ።

ኘ. የሕብረት ሥራ ሥነ ሥርዓት በእግዚአብሔርና ከዚህም በቀር ባገር ውስጥና በውጭ አገር ተወዳጅ ነው ስለዚህ ያዘማማም የጸናጽል አ ወራረድ የማስረገጥ የከበሮ አመታት የመዘምራን አለባበስ በኅብረት በአንድ ዓይነት እንዲስማማ ቢደረግ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው አገልግሎት ያማረ ይሆናል ።

አ. መጻሕፍት ንዋያተ ቅዱሳት በሚገባ እየተጠበቁ ሊተረጐሙ የሚገባቸውም ባህል ትምህርት ወይም ታሪክ ነክ የሆኑት ጽሑፎች ሁሉ እየተተረጐሙና እየታተሙ አዳዲሶች ድርሰቶችም ለአዲሱ ዘመን ትውልድ እንዲዳረሱ ማድረግ ከቤተ ክርስቲያን ይፈለግባታል ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያኖች ቤት ስለሆነች የምትጠነክርበት የሥራ መስክ በየረድፉና በየአግጣጫው ሰፊ ስለሆነ ወደዚሁ ሁላችንም እንሠማራ ።

## የሠራተኞች ኃይል......

ከ፲፬ኛው ገጽ የዞረ

ሚመጣ የዛሬውን የሥራ ውዝፍ ዛሬ ሠርቶ ማጠናቀቅ እንጂ ለነገ ማስተላለፍ ይቅርታ የማይገኝለት ኃጢአት ነው እንደተባለውም ዛሬ ካልሠሩበት ትናንት ስለሚሆን ከልዩ ልዩ ሥራና አገልግሎት ጋር አይገጣጠምም በርናርዶስ የተባለውም ሊቅ ዛሬ ትሠራው ዘንድ የሚቻልህን ለነገ ለምን ታሳድራለህ የሚመጣውም ጊዜ በሥልጣንህ ሥር እንዳይደለ አስተውል መልካም የሆነውንና ለሕይወትህ የሚያስፈልግህን ሁሉ ትሠራበት ዘንድ የምትችልበት ያንተው ጊዜ ዛሬ ነው" ሲል ማንኛውም ሰው ዛሬ ሊሠራ እንደሚገባው ምክሩን ለግሦአል ።

አባባሉም መልካም ነው ጊዜን ተከትሎ መሥራት ዕውቀት ፣ ገንዘብ ፣ ዘዴ ከኃይል ጋር ተባብረው ጥቅምን ሊያስገኙ ይችላሉ እነዚህም የእንቅስቃሴና የለውጥ ምልክቶች ናቸው ። ነገር ግን ሳይሠሩ ጊዜ ባፈራው ብቻ እየተጠቀሙ የመጀመሪያ ነኝ እያሉ ሐተታ ማብዛት ወገኛ መሆን ነው ።

ተከታዩን በገጽ ፳፮ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ካህናቶቻችን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ከሌሎች ካህናት ፍጹም የሆነ ልዩነት አላቸው፤ ይህም ማለት የተለየ ባሕልና አቋም በኅብረተሰቡ መካከል የላቸውም ። ከጥንት ጀምሮ የነበረውን ታሪክ ስንመለከት ካህናቱ የሕዝቡ ባሕል ባሕላቸው ሀገሩ ሀገራቸው ታሪኩ ታሪካቸው በመሆኑ ከመደበኛ የክህነት ሥራቸው በላይ በትምህርት በግብርና በኪነ ጥበባትና በሌላም ተግባራት ውስጥ ሁሉ ራሳቸውን እያስገቡ ሕዝቡን ሲመሩና ሲአገለግሉ ቆይተዋል ወደፊትም ያገለግላሉ ።

አንዳንድ የውጭ ሰባኪዎች ወደ ሀገራችን ሲገቡ አስቀድመው የሕዝቡን ባሕልና ቋንቋ ማጥናት ግድ ይሆንባቸውና ያጠናሉ ጥናታቸውም የራሱ የሕዝቡ የሆነውን ባሕልና እምነት ለማስፋፋት ሳይሆን የራሳቸውን ሃይማኖትና ባሕል ለማፈናጠጥና የጥንቱን ባሕልና ሃይማኖት ለመበከል ነው ።

በሀገሪቱ ላይ ጠላት በመጣበት ዘመን ሁሉ የተካሄደውን የትግል ታሪክ ስንመለከት አንዳንድ የውጭ ካሕናት (ሚስዮናች) ለሚመጣ ጠላት የመግቢያ ስልትና ዘይቤውን እያሳዩ ትግሉም ተፋፍሞ ጠላት ሊሸነፍ ሲቀርብ የክህነት አርማቸውን ወደ ወታደር እርማ ፣ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ወደጦር መሣሪያ ለውጠው ወግተውናል ።

በጊዜአችንም በኑሮው የተጐዳውና የተረገጠው መብቱ ተነፍጎት መብቱን ለማስመለስ የሚታገለው ሰፊው ሕዝብ ሲንቀሳቀስ ጠላትነታቸውን ለመሰወር የነበራቸውን ድርጅት እየዘጉ ወደ ሀገራቸው የገቡ ጥቂቶች አይደሉም ።

ከካህናቶቻችንም መካከል አንዳንድ ለግል ጥቅም የቆሙ ከገዥው መደብ ጋር ተጣብቀው ከሕብረተ ሰቡ አጥቂዎች ጋር ተባብረው የነበሩ ግለ ሰቦች እንደነበሩ ባንክድም ብዙኃኑ የገጠሩ ካህናት ግን ከሕዝቡ ጋር ጦርና ጐራዴ እየመዘዙ የሀገራቸውን ዳር ድንበር ላለማስደፈር ደማቸውን እንዳፈሰሱና አጥንታቸውንም ለሀገራቸውና ለአንድነታቸው ክብር ማጣፈጫው አድርገው የከሰከሱ ናቸው ። ይህንም እንዲአደርጉ የተገደዱበት ሕዝቡ ፣ ሕዝባቸው መከራው መከራቸው ፣ ባሕሉ ባሕላቸው ፣ ቋንቋው ቋንቋቸውና ሃይማኖቱ ሃይማኖታቸው በመሆኑ ነው ።

የኢትዮጵያ ካህናት እንደሌላው ፣ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ 6 ዕለታት ሁሉ እጃቸውን አጣምረው የሰንበት ሙዳይ በማዞር ብቻ ለሌላው ምዕመን ሸክም አይሆኑም እንደ ሐዋርያው ቅ.ጳውሎስ ራሳቸውን በተግባረዕድ ለመርዳት እንደነ ኤልያብ ዕደ ጥበባትን መሥራት እንደ አቤል ከብቶችን በማርባት እንደነ ኢያሱ ጠላትን በመዋጋት እንደነታዴዎስ እርሻን በማረስ የተፈጥሮ ሥራዎችን በማከናወን ራሳቸውንና ሕብረተሰቡን ይረዳሉ ።

ያቅዱሳን እረፍታቸው አምላክን ማመስገናቸውና ምዕመናንን ማገልገላቸው ነው እንደ ተባለው ሁሉ የእረፍት ጊዜአቸውን እንኳን በእረፍት ሳያባክኑ ከማታ እስከ መንፈቀ ሌሊት ፣ ማሥ በመግሠሥ ቅኔ በመዝረፍ ዜማ በማስተማር ያሳልፉታል ። ቀኑ ነግቶ ወደ ሥራ እስኪሠማሩ ድረስም ቅኔ በማስነገር ዝማሬ ማዋስዕቱን በማስተማር ሕብረተ ሰቡን ያገለግላሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ብራና በመፋቅ ቀለም በመበጥበጥ እየጻፉና እየመዘገቡ የተውልንን ቅርስ በዓይናችን ስንመለከተው ሀገራችንን የኪነት ባለሙያና የሥነ ጹሑፍ ባለቤት አድርገዋታል ።

በአንጻሩ ወደ ሀገራችን የሚገቡ (የውጭ ካህናት) አንዳንድ ሚሲዮናች ስንመለከታቸው ለሀገራችን ቅርስ የሚሆን ሊአበረክቱ ይቅርና ካህናቶቻችን ያበረከቷቸውን ቅርሶች በስውርና በቀጥታ ወደሀገራቸው በማጓዝ እንደበዘበዙን በውጭም ሆነ በውስጥ ይመሰክርባቸዋል ።

ካህናቶቻችን የተፈጥሮ ደን ሀብታችንንም የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ዜግነታቸው ስለሚአስገድዳቸው በየደብሩና ገዳማቱ ዛፎችን እያስተከሉ የደን ሀብትን በመንከባከብ እያስጠበቁ ቆይተዋል ።

እንዳይቆረጥ የተለያዩ ትምህርቶችን ይሰጡ ነበር ለመካኑ በልጅ አምሳል የስምህ መጠሪያ ይሆንሀል በማለት ለወላጁም አትክልትና ልጅ አንድ ነውና እንደ ልጅህ አድርገህ ተንከባከበው በማለት ያረንጓዴ መቀነት ዘመቻን አስቀድመው ተልመውት ነበር ።

ዛሬም ቢሆን በገጠር ያሉት ካህናቶቻችን ከሀገራቸው ፍቅር ከመቃጠል ያልበረደ አእምሮአቸው ከእርፍና ከማጭድ ያልተወገደ ዕጃቸው ከስብሐተ እግዚአብሔር ያልተላቀቁ ልሳናቸው አገልግሎቱን ሳያቋርጥ በሰፊው እርሶ አደር መካከል የወንዝ ሳቢሳ መስለው ይኖራሉ ።

በከተማችንም ያሉት ካህናት ካንዳንድ ወገበነሎች በስተቀር በዐበይት በዓላት ንዑሕ ወንጌልን በማስተማር ፣ በአዘቦቱም ዕለት በየመንደሩ መጠለያ እየሠሩ ሕፃናት በማስተማር ለሕብረተ ሰቡ የሚሰጡትን አገልግሎት እንደ ቀጠሉ ናቸው ።

በሀገራችንም ላይ በተቃጣው የእምፔሪያሊስት ጦርነት ከሰፊው ሕዝብ ጋር ሆነው በመሰለፍ እንደ አቡሚሌክ የኢትዮጵያን ክብር መደፈር አታሳዩን እያሉ ከኢትዮጵያ ድንበር መደፈር በፊት የራሳቸውን ሕይወት አሳልፈው የሰጡ ካህናቶች ጥቂቶች አይደሉም ። በጅጅጋ ሜዳ ከጠላት ጋር ተናንቀው ሕይወታቸውን ለሀገራቸው ፍቅር አሳልፈው ከሰጡት ውስጥ ኢትዮጵያን በደማቸው የዋጅዋትን የጀግናውንና ኢትዮጵያዊውን ዳግማዊ ናቡቴ የጅጅጋውን መምሬ መላኩን በዚህ አጋጣሚ እናስታውሳቸዋለን ።

እኒህ ወገናችን ታላቅ ካህን በአድዋና በማይጨው አባቶችን ካህናት የሠሩትን ታሪክ እንደገና ከዕንቁና ከአልማዝ ውድ በሆነው ሕይወታቸው አድሰውታል አጉልተውታል ።

በየገጠሩ ሜዳ ተሰልፈው ከሞት የተረፉትም ካህናት በድንኳን መስሎኝ ምድራዊ መኖሪአችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በሰው እጅ ያልተሠራ በእግዚአብሔር የተሠራ ዘላለማዊ የሚሆን ሕንፃ እንዳለን እናውቃለን'' 2ቆሮ3-1 ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተማረውን የእምፔሪያሊስት ሐዋርያት ዶክትሪን እንደሚተረጕመው ሳይሆን አባቶቻችን ሊቃውንት በመንፈስ ተርጉመው እንዳስተማሯቸው ሀገራቸው ኢትዮጵያ የፀጋ ዘመናቸውን አሳልፈውበት በፀጋ ለተሰጧቸው ልጆቻቸው የሚአወርሷት በመሆኗ የዓለም ነፋስ የሆነው ጦርነትም ሆነ ሰይጣን የሆኑ ቅኝ ገዥዎች ነካክተው እንዲአሳድፏት አይፈቅድም ይህም ጠባያቸው ለሀገራችን ካህናት ከዓለም ካህናት የተለየ መታወቂያቸው ነው ።

ይህም በመሆኑ ጥቅሱን በፊደል በመተርጐም የታሪክ ነጋሪ አዛውንት ሽማግሌና ባልቴቶችን ሲጨፈጭፍ ዝም ብለው ሊመለከቱ ባለመቻላቸውና ባደረጉትም ተጋድሎ ከሰፊው መደበኛና ሕዝባዊ ሠራዊት ጋር አንድነታቸውን አጠናክረው በመነሳታቸው አሸናፊ ሆነው እነሆ ዛሬ ''ብፁዕ ውእቱ ዘይሬኢ ድቀተ ፀሩ'' በማለት የጠላቱን መውደቅ የሚያይ ብፁዕ ነው የሚለውን ቃል ደጋግመው ይናገሩታል ።

ቤተ ክርስቲያናችን እንደሌሎች ጦርነትን ባርካ ብዙ ሕዝብ እንዲአልቅና አንዱ ላንዱ ቅኝ ተገዥ እንዲሆን ፈጽሞ አትመክርም የራሷ ምዕመናንም የሰፈሩባት ኢትዮጵያ በቅኝ ገዥዎች እጅ እንዳትነካም ስለምትፈልግ ስንኳን ነፍስ ያለው ወንድ ይቅርና ሀገራችን በጠላት ስትወረር በመቃብር ቤት የዘጋች መነኩሲት በያዘችው ምርኩዝ አለመከላከል ከጽድቅ ገብቶ የሚ

ተከታዩን በ፳ኛው ገጽ ይመልከቱ



# የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመንበረ ፓትርያርኩን እንደገና መቋቋም ፷ ዓመት አከበረች

**የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 60 ኛውን የመንበረ ፓትሪያርክ እንደገና መቋቋም በታላቅ ሥነሥርዓት ማክበርዋን ከመስኮ የተገኘው ዜና አብሥሯል ።**

ይህንኑ ታላቅ በዓል ምክንያት በማድረግ ፓትርያርክ ፒመን ባደረጉት ንግግር የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪካዊ አመጣጥ ከጠቀሱ በኋላ እ.አ.አ. በ1721 ዓ.ም. በታላቁ ጴጥሮስ ተጨቁና ቆይታ እ.ኤ.አ. በ1917 እንደገና መቋቋምዋን አስገንዝበዋል ።

እ.ኤ.አ. በጥር 23 1918 ዓ.ም. የሶቪዬት መንግሥት በወጣው ህገ መንግሥት መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የተለየች መሆንዋን ጠቅሰው ይህ ድርጊት በቤተ ክርስቲየኒቱ ሕይወት ውስጥ አዲስ ለውጥ ማምጣቱን አውስተዋል ።

በኒህ ታላቅ በዓል ላይ እንዲገኙ የተጠሩ መልእክተኞች ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የፕሮቴስታንት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፣ ከሌሎችም አህጉራዊ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች መላካቸው ታውቋል ።

ፓትሪያርክ ፒመን ጨምረው ሲናገሩ ፣ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ''የቤተ ክርስቲያናትን አንድነት ፣ ዓለም አቀፋዊ ሰላም ፣ የኤኮኖሚን ሚዛን መስተካከል የጦር መሣሪያዎችን መቀነስ ትሻለች ትደግፋለችም ብለዋል'' ሲል ኤኮሙኒካል ፕሬስ አስታውቋል ።

## መንፈሳዊ ድርጅት ጉዳተኞችን ሲያቋቁም

አደጋ በሚደርስበት ወቅት ቀልጠፍ ያለ እርዳታ ሊገኝ ይቻላል ። ዳሩ ግን አደጋ የደረሰባቸውን ሰዎች ማቋቋም ሆነ በልማት ተግባራት መስክ የማሰማራት ጉዳይ ቀላል አይደለም ። በህንድ የእርዳታ ማስተባበር ተግባር ዲሬክተር የሆኑት ሻለቃ ማይክል ይህን እውነት ሆኖ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ተገንዝበውታል ስለሆነም ባለፈው ህዳር ወር አንደሃራ ፓራዲሽን አውሎ ነፋስ በመታው አገሪቱ በተጥለቀለቀች ጊዜ ዲሬክተሩ ከባንክ የብድር ገንዘብ ተቀብለው ጉዳተኞቹን በመርዳት ረገድ አላቅማሙም ። ይህንንም ተግባራቸውንም በመደገፍ ብዙ ያገርና የውጭ በጐ አድራጊዎች እንደሚደግፉዋቸው ያምኑ ነበር ።በዚሁ አንፃር ሠራተኞቻቸው በሚገባ እርዳታውን አካሄዱ ። እውነትም ብዙ እርዳታ ሊያገኙ ችለዋል የሻለቃው ትጋትና የሠራተኞቹም ህብረት በተጨማሪነት ለመጡት ቡድኖች መልካም ምሳሌ ሊሆን ችሏል ። ሁኖም ይህ ለድንገተኛ አደጋ የተመደበው እርዳታ ካበቃ በኋላ የመቋቋሙ ጉዳይ አለ ። ይህንንም ለማቃለል ሻለቃ ማይክል በቅርቡ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ ልዩ ልዩ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን ጐበኙ ይህንንም ማድረጋቸው በጐ አድራጊዎችን አብያተ ክርስቲያናትን ፣ የማኅበራዊኑሮ ክፍሎችን በማቋቋሙ ተግባር ላይ ለማሳተፍ የሚቻልበትን ዘዴ ለመፈለግ ነበር ።

በነገራችን ላይ ይህ የማቋቋም ድርጅት በተፈለገለት አካባቢ በህንድ የሚገኘው የበጐ አድራጐት ድርጅት የማቋቋሙን ፕሮግራም የሚያካሂድባቸው በ20 መንደሮች ሲሆን እያንዳንዱ መንደር ከ1000-1200 ኑዋሪዎች አሉት ። መንደሮቹ ከዋና መንገዶች በመራቃቸውና እርዳታም ሊደረግላቸው ስለሚገባ ተመርጠዋል ። የማቋቋሙ ምርጫ በተጨማሪ የሚያተኩረው በመንደሮቹ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ባላቸው የልማት ሥራ ተሳታፊነት ጭምር ነው ።

የልማቱ ፕሮግራምም የሕንፃ ሥራን እርሻን የቤት ውስጥ እንዱስትሪዎችን ያጠቃልላል አንዱ ተፈላጊ ነገር በያንዳንዱ መንደር ጠንካራ የሆነ የአውሎ ነፋስ አደጋ ቢመጣ ኑዋሪዎቹ ሊጠለሉባት የሚችሉ መኖር አለበት የሚል ነው ። ይህ ማዕከላዊ ህንፃ ከመጠለያነቱ ሌላ ለትምህርት ማዕከል ፣ ለመለስተኛ እንዱስትሪ ለእጅ ሥራ ለሕፃናት ጤና ጥበቃና ለሌሎችም የህብረተሰቡ ግልጋሎት ይረዳል ። ከዚህም በስተቀር በያንዳንዱ መንደር መሀል ሁለት የውሃ ጉድጓዶች ይኖራሉ ። በተጠቀሰው አደጋ ከተጐዱት ሰባ በመቶ የሚሆኑት ሥራ የሌላቸው የቀን ሙያተኞች መሆናቸው በተደረገው ጥናት ተረጋግጧል ።

በነዚህ ሰዎች አካባቢ የሚካሄደው የማቋቋም ተግባር ሦስት ላይ ይመደባል አንደኛው የጓሮ ልማት የውሃ ቦዮች ቁፋሮ ጥርጊያ መንገድ ማዘጋጀት ትንንሽ ድልድዮችንና ለድሆች ሰዎች የሚሆኑ ቤቶችን መሥራት ነው ። እዚህ ላይ የእርዳታ ማስተባበሪያው ድርጅት ቀደም ሲል ለተጐዱት ሰዎች መጠጊያ 13.000 ቤቶችን ሠርቶአል ።

ሁለተኛው ፕሮግራም የህብረተሰቡን አቋም ከኤኮኖሚ አንፃር (ሲሲዩ-ኢኮኖሚክ) እና የበጐ አድራጐት ተግባራትን ማለትም እንደ ቤተሰብ ትምህርት የህፃናት መርጃ አመጋገብ ለወላድ እናቶች እርዳታ ማድረግን ይመለከታል

የኤኮኖሚው ተግባራት የገንዘብ ገቢ ሊያስገኙ የሚያስችሉ ሥራዎችን ከብት ርቢን ዶሮ ርቢን ፣ ሌሎችንም የጐጆ ውስጥ እጅ ሥራዎችንና የህብረት ሥራዎችን ያጠቃልላል ።

ሦስተኛው እቅድ በልማቱ መስክ የመሪነትን ችሎታ ማዳበር ጉዳይ ነው ይህ ለህብረተሰቡ እድገትና እርምጃ በጣም የሚረዳ ነው ።

የማቋቋሙ ተግባር ዲሬክተር ስለጠቅላላው ሁኔታ ሲናገሩ ፣ ''ክርስቶስ ያሳየውን በጐ ተግባር ልንከተል እንሻለን፡ ማለትም ማሳየት መቀስቀስ ማሳተፍ'' አለብን ሲሉ ተናግረዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የእግዚአብሔር ሐላዌ

ከቁስ መክብብ አጥናው

"ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔር የለም ስትይ ኖረሽ ያለ እንደሆን ወዮልሽ ። አለ ስትይ ኖረሽ ባይኖር ግን ምንም ዓይነት ዕዳ በደል አይኖርብሽም ፤ ከኃጢአት ነፃ ነሽ" ሲል አንድ ከፍተኛ የሳይንስና የፍልስፍና ተመራማሪ ሊቅ የተናገረው ቃል ለዘለዓለሙ የሚታወስ ሕያው ነው ።

በመሠረቱ በእግዚአብሔር ህላዌ ማመን ሰውን ከሥልጣኔ ዕድገት ወደኋላ ያስቀረበት ዘመን የለም ። አለማመን ደግሞ ማንንም ከማን እንዲበልጥ አላደረገውም ። በእግዚአብሔር ሕላዌ ከሚያምነው ኅብረተሰብ መካከል ብዛታቸው ከቶ ሊቆጠር የማይችል ለመላው ዓለም የሰው ዘርና ሕይወት ሌላውም ፍጥረት ሁሉ የደህንነት ዋስትና የሚሆን እጅግ ብዙ የፍልስፍና የሳይንስና የቴክኖሎጂ ጥበብ ያበረከቱ መኖራቸው የማያጠራጥር ሐቅ ነው ። በእግዚአብሔር ህላዌ ማመናቸው ፍጥረትን ለመቆጣጠር የሚያበቃና ይህን ዓለም ለመለወጥ የሚያስችል የረቀቀ ጥበብ ከማግኘት አላገዳቸውም ። እየረ እየራትን ዕመቀ ዕመቃትን ጠልቀውና ዘልቀውገና በዓይን ያልታዩና በእጅ ያልተዳሰሱ አዳዲስ ዓለማትን (ፕላኔቶችን) መርምረው ምንነታቸውን ከማወቅ አልገታቸውም ። እንግዲያውስ የማንም ሰው ከፍተኛ የዕውቀትና የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃ የሚለካው በማመንና ባለማመን ሊሆን ከቶ አይችልም ።

አንድ አንድ ግለሰቦች "እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አትመራመሩ ይላል" የሚል አፈታሪክ ሲናገሩ ይሰማሉ ። ነገር ግን "አትመራመሩ" የሚል ቃል የሃይማኖታችን መምሪያ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ተፈልጎ አይገኝም ። እንዲያውም መጽሐፋችን ሁሉን መርምረን እንድናውቅ የሚያበረታታ ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ አለን ።

ለምሳሌ ሁሉን መርምሩ የተሻለውንም መርጣችሁ ያዙ ተብሏል በሌላም በኩል አጽንዖዋ ለጥበብ ከመኢይትመአዕ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳይቃጠል ጥበብን መርምሩዋት ። አፉሁ ለጻድቅ ይትሜሐር ጥበበ የጻድቅ ሰው አንደበቱ ጥበብን ይማራል ዕውቀትን ይመረምራል" ወዘተ የሚሉ ቃላት በዳዊት መዝሙር ተጽፈዋል ። እንዲሁም በትንቢተ ዳንኤል "ዳንኤል ሆይ አንተ ግን እስከፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ መጽሐፉንም አትም ፤ ብዙ ሰዎች ይመራመራሉ ዕውቀትም ይበዛል" ተብሎ በእግዚአብሔር መንፈስ የተነገረ ቃል እናገኛለን ። እንግዲህ ሐቁ ይህ ከሆነ እግዚአብሔር አትመራመሩ ይላል የተሰኘው አፈ ታሪክ ከየት ተወለደ ? በዚህም ደግሞ አንደኑትም ። ቁንጽል አመለካከት ያላቸው ግለሰቦች ከእውነተኛው ሣይንሳዊ ፍልስፍና ይልቅ አፈ ታሪኮችን በማጋነን ዕውነትን መሠወር ልማዳቸው መሆኑ ግልጽ ነው ።

እውነተኛው ሳይንስማ ሰውን እግዚአብሔርን ወደማወቅ ደረጃ የሚያደርሰው መሆኑ ከዘመናችን በፊት ተፈትኖ የታወቀ ነው ። ሣይንስ ራሱ የፍጥረትን ሒደት መቆጣጠሪያ ኃይል ሲሆን ፍጥረት ደግሞ የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራዎች መንጸባረቂያ መሆኑን ላይብኑት የተሰኘው ጀርመናዊ ፈላስፋ ሲገልጥ "በፍጥረት ሁሉ ላይ የሚታየው አስደናቂ የጅጥበብ ሥራም ስለእግዚአብሔር መኖር በግልጽ የሚመሰክር ነው" ብሏል ። ሌላው ፈላስፋ (አርበርት የተባለው) ደግሞ የእግዚአብሔርን መኖር የዚህ ዓለም አፈጣጠር ድንቅ ሥራ ይገልጠዋል' አለ ። ፈላስፋው አርስቶትል ደግሞ "ማናቸውም የሚነቀንቅ (ተንቃናቂ ነገር) የግዴታ አንድ ነቅናቂ ሊኖረው ያስፈልጋል ። ስለዚህም ለሁሉም ነገር መነሻው ምክንያት እግዚአብሔር ስለሆነ እግዚአብሔር ባይኖር ግን ይህ ዓለም ራሱ አይገኝም ነበር" ሲል ጽፏል ።

ኢራቅሊጦስ የተሰኘውም ፈላስፋ "እግዚአብሔር ለፍጥረት ሁሉ ሕይወት ነው" በማለት ሲገልጠው ሌላው ፈላስፋ ደግሞ "ብርሃን ከፀሐይ እንደሚፈልቅ ዓይነት እንዲሁም ዓለም ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው ይለዋል ። እንግዲህ ይህንና ይህንንም የመሰለውን ግልጽ የሆነ ሐቀኛ ማስረጃ በጽሑፍ ቀርጸው ትተውልን ያለፉ ታላላቅ ሊቃውንት እያሉን ዛሬ ጥልቀት በጎደለው አመለካከት የእግዚአብሔርን ህላዌ ለማካካድ የሚሞክሩ ቢኖሩ ለአባባላቸው ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖረውም ። ይህ ዐቢይ ጉዳይ ከዘመናችን በፊት ተመርምሮ እያሌ ሊቃውንት ግራ ቀኙን አይተው የእግዚአብሔርን ህላዌ አምኖ መቀበል እንደሚገባ አረጋግጠውልን አልፈዋልና ነው ።

---

## ሰው ከእግዚአብሔር አፍ

## በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ

## ብቻ አይኖርም ።

**ማቴ. ፬ ፡ ፬**

---



# ልማድ ሃይማኖት አይደለም

ባለፈው ጽሑፋችን እንደገለፅነው ሁሉ የልማድ ዓይነት ሁለት ሲሆን ይኸውም መጥፎ ልማድና ጥሩ ልማድ ነው ። ብለናል ።

ከነዚህም መሃከል ሃይማኖትን መስለው በህብረተ ሰቡ መኸል ሰርገው ከገቡት መጥፎ ልማዶች አንዳንዶቹን ብንጠቅስ አንዳንድ የመጥፎ ልማድ ተገዥዎች መተዳዳሪያ አድርገው የያዙት ሰው ሲሞት አስለቃሽ ሆነው መኖር ሲሆን ይህም ከጥንት ጀምሮ መጥፎ ልማድ ሆኖ የመጣ ሃዘንተኞቹ የወገናቸው የመለየቱ ሃዘን እንዳይበቃቸው ባስለቃሾቹ ምክንያት ተገልጦ የማያውቀውን ገላቸውን ገልጠው በመደብደብ በሚመጣው በሽታ የሚጠቁ ሰዎች ብዙዎች ናቸው ።

ይህም ድርጊት እያወቁ የሚያጠፉት ሲሆን ሌሎቹ ግን የሃይማኖት ግዴታና ያለ ሙሾ አውራጅ የሞተውን ሰው ማስቀበር ሃፍረትና ፀያፍ መስሎ ስለሚሰማቸው ገንዘብ ባይኖራቸው እንኳን ተበድረው ሙሾ አውራጅ ይቀጥራሉ ። እዚህ ላይ እንግዲህ ልንገነዘበው የሚያስፈልግ እነዚህ ሰዎች ከገንዘባቸው አልሆኑ ወይ ከጤንነታቸው አጉል ችግር ላይ የሚወድቁ ብዙዎች መሆናቸውን ነው ።

ቤተ ክርስቲያንም ይህ ሥራ መጥፎ ልማድ እንጂ ሃይማኖት እንዳልሆነ በሲኖዶስ ወስና ነበር ቢሆንም ተቀባይ አላገኘችም ። በአሁኑ ጊዜም በአንዳንድ አካባቢ በቀበሌና በሰበካ ጉባኤ ትብብር ይህንን መጥፎ ልማድ ለመተው በመስማማት ላይ መሆናቸው በመገናኛ ዘዴ እየተገለፀ ነው ። ይህንንም አርአያ ሌሎቹ ሁሉ እንዲከተሉት የሁላችንም ምኞት ነው ። ሞት (እረፍት) ምንም እንኳን የአሟሟቱ (የማረፉ) ሁኔታ ቅደም ተከተል ቢኖረውም ለማንኛችንም የማይቀር ዕዋ መሆኑን ማመን አለብን ። ካመን ዘንድ ደግሞ የመጥፎ ልማድ ተገዥዎች በመሆን ከምንታመም ይልቅ ጤንነታችንን ጠብቀን ጥሩ ሥራ እየሠራን በተራችን ብንሄድ የበለጠ ነው ።

ሌላው መጥፎ ልማድ ደግሞ አንዲት ክርስቲያን እመጫት ሰው ሊጠይቃት ሲመጣ ቤቷ ጠበል ካልተረጨ በስተቀር ያ ጠያቂው ሰው ጠይቋት ሄዶ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት አይችልም። ይህ እንግዲህ መጥፎ ልማድ ነው ? ወይንስ ሃይማኖት ? ይህ እንኳንስ ሃይማኖታቸው ሌላ ለሆኑትና ለባለ ሃይማኖተኞቹ እንኳን በጣም የሚያስጠላ ነው። እግዚአብሔር ራሱ በተቀደሰው ትእዛዙ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ብሎ ያዘዘውንና በሔዋን ስህተት የተዘጋውገነት በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማካኝነት ተከፈተልን ብለን የምናምነውን አንዳንድ የመጥፎ ልማድ ተገዥዎች ከትእዛዝ ውጭ እንደ ወለደችና በማርያም ድንግል ምክንያት ደህንነት እንዳላገኘን አስመስለው ከላይ እንደገለፅነው ሰውን ሲያሳስቱ ይታያሉ ።

ነገር ግን ልናውቀው የሚገባን እግዚአብሔር ሰውን ይበልጥ የሚያነጋግረው በልቡ ናው በኩል ንፁህ ሁኖ ሲቀርብ ነው ። ምስጢሩንም ሁሉ የሚገልፅለት ሊያውቀው ሳይሆን ሊወደውና አምኖም ሊቀበለው በንፁህ ልቦና የመጣውን እንጂ እግዚአብሔር ልብንና ኩላሊትን የማይመረምር አስመስለው ከሌላው ከከፉ ስራቸው ሳይነፁ ካራስ ቤት ሳይረጭ ገብቶ ቤተ ክርስቲያን መግባት ማርከስ ነው ብለው እንደሚያወሩ የመጥፎ ልማድ ተገዢዎች ዓይነት ያለ መሆኑን ነው ። ሃይማኖት ከማመን በፊት መመራመርንና ሞክሮ ማየትን አትቃወምም ይልቁንም የምትመክረን መጀመሪያ አይተንና መርምረን ተመልክተንም እንድናምን ነው እንጂ ለዚህም በቂ ማስረጃ የሚሆነን ዮሐ.ም.5 ቍ.39 ትንቢተ ዳንኤ. ም. 12 ቍ. 4 ብንመለከት ከቃሉ ብዙ መማርና ማወቅ እንችላለን አንዳንድ የመጥፎ ልማድ ተገዢዎች ግን ሽፍንፍን ልማዳቸው እንዳይገለጥባቸው ስለሚፈሩ ሃይማኖት መመራመርን የማትፈቅድ አድርገው ያወራሉ ። የእነሱ ማውራት ግን እውነቱ በእውነተኞች ሃይማኖታውያን እስኪገለጥ እንጅ ዘላቂ አይሆንም ።

የመጥፎ ልማድ ዓይነቱ በዚህ ብቻ አይበቃም አንድ አጭር የመጥፎ ልማድ እውነተኛ ተረት እንንገራችሁ ። አንዲት ሴት በየጊዜው ድስቷን ውሻ እየላሰ ያስቸግራት ነበርና በላሰው ቍጥር ድስቷን እየያዘች ንስሐ አባቷ ጋ (ካህን) እየወሰደች ታስባርክ ነበር ። ከእለታት አንድ ቀን ቄሱ (ካህኑ) ስልችት ስላላቸው ልጄ ካልሆነ ውሻውን አምጭና አፉን ልባርክልሽ አሏት ይባላል። እንግዲህ አንባብያን በማን ትፈርዱ ይሆን በሴቷ ወይንስ በካህኑ ? መቸም የፍርድ ነገር ያስቸግራልና የናንተም የኛም ፍርዳችን ለየቅል ሊሆን ይችላል ይህቺ ሴት ካለመማሯና ካለማወቋ የተነሳ እንደ ሃይማኖት ሆኖ የቆየት ያውመጥፎ ልማድን አጥብቃ በመያዟ በንፁህ ሕሊናዋ ቄሱን ልታስለች በቃች እንጂ ብታውቅማ ኑሮ በኢቃ ማጠቢያ መርዝ አጥባ ድስቷን ትጠቀምበት ነበር ። እግዚአብሔር ለንፁሐን ሰዎች ቅርብ ነው ለአባቶቻችን ቅዱሳን ይገልፅላቸው እንደነበር አሁኑም ለእውነተኞቹ ሃይማኖታውያን በመንፈስ ይታያቸዋል ። ሁላችንም ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር የምንፈልግ ከሆነ ከመጥፎ ልማድ መራቅ አለብን ። ከዚህም የምንርቀው ብዙ የኦርቶዶክስ ድርጅቶች አሉ ሄደን እናነጋግራቸው ሥራቸው ይህ ስለሆነ ከነርሱ ብዙ ለመማር እንችላለን ዋጋ አይከፈልበትም በነፃ ነውና ከዚህም ሌላ ከነዚህ ድርጅቶች እየተዘጋጁ የሚሸጡ መጽሔቶችና ጋዜጦች አሉ እነርሱንም እየገዛን እናንባቸው ከነርሱም ብዙ ጥቅም እናገኛለን ከስህተታችንም ከሞላ ጎደል ለመታረም እንችላለን ።

አንባብያን በስም ሃይማኖተኞች ነን

ተከታዩን በ፳ኛው ገጽ ይሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ካህናቶቻችን

ከ፲፮ኛው ገጽ የዞረ

ቁጠር አለመሆኑን ስለምታምንበት ቁስ መነኩሴ ሁሉ ሀገራችን ከጠላት ፈተና እስከተገላገለች ድረስ ትጥቃቸውን አይፈቱም ።

በአንጻሩም ደግሞ በክህነታቸው ቤተ ክርስቲያን ሳትመርጣቸው በሙያቸውና በመንፈሳዊ አቋማቸው ሳይታመንባቸው ፣ በየቤተ ክርስቲያኑ መቃብር ቤትና በቤተ ክህነቱ ውስጥ ተመስገው ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት እንቅፋት ለንጹሑ ኢትዮጵያዊ ካህን ስም ጥፋት ለሕዝበ ክርስቲያኑ የመቀመጫ ብጉንጅ ሆነው የሚአስቸግሩ እንዳሉ በየቤተ ክርስቲያኑ ይነገራል ።

ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ ጽ ቤት የተቀላጠፈ ሰባክያንን የማስማራት ኃይል ያለው መመሪያ የመንደፍና የማዘጋጀት ችሎታ የሌለው ፣ መሆኑን ቢአሳይም ፦እንዲህ ያለ ጠባይ ያላቸው ግለ ሰቦች በነቃውና የማስተዋል ኃይሉ በዳበረው ሕዝበ ክርስቲያን እየተወገዙ ከመውጣታቸው በፊት አሁኑኑ በሙያቸውና ባቋማቸው እንጸር ራሳቸውን ለመርዳት የሚችሉበትን መንገድ ለማግኘት ቢሞክሩ ታላቅ ማስተዋል ነው ።

"በከንቱ ያለዋጋ ያገኛችሁትን በከንቱ ያለ ዋጋ ስጡ" በሚለው አምላካዊ መመሪያ መሠረት የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ካህናት በመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ዋጋዬን አገኛለሁ የሚሉት ከሚአገለግሉት አምላክ እንጂ ስብሐተ ንግህ ቁሜ አለሁ ፣ ቀድሻለሁ ዋጋዬ ይሰጠኝ በማለት የሚጠይቁት ግለ ሰብ የለም ። አገልግሎታቸውን የሚአበረክቱት በመንፈስ ለሚአገለግሉት አምላክ ስለሆነ ዋጋቸውም መንፈሳዊ ነውና በሃይማኖቱ አንፃር ይመለከቱታል ።

ራሳቸውንና ቤተ ሰቦቻቸውን የሚረዱት ከሰፊው አርሶ አደር ጋር በወንፈል በደቦ በግልም እየተሰማሩ በሚአመርቱት በጉልበታቸው ዋጋ ነው እንደ ዳዊት በመንፈሳዊ ክንዳቸው ኃይለ አጋንንትን እየሰበሩ በሥጋዊ ክንዳቸው የጉልያድ የግብር ልጆቹ ቅኝ ገዥዎችን እያሸነፉ በክህነታዊ አቋማቸው ለእርሱ ያልሆኑትን ይልቁንም ስለ ቤተ ሰቦቹ የማያስብ ምዕመን ካለ ከሁሉ የሚከፋ መሆኑን ቅ.ጳውሎስ እንዳስተማረ ሁሉ እነሱም ስለሀገሩ ስለድንበሩ ስለ ዜጋው ለማያስብ ማንም ኢትዮጵያዊ ምዕመን ካለ ከሁሉ ይልቅ የከፋና ኃጢአተኛ መሆኑን እያስተማሩ ወደፊት ይራመዳሉ ።

ካህናቶቻችን ሥራቸው ሐዋርያዊ ዘመቻ መሆኑን ስለሚአምኑም ምንጊዜም ቢሆን ዘማቾችና ባላቸው ችሎታ መአይምነት ከሕብረተ ሰቡ መካከል እንዲደመሰስ በየዛፉና በየጥላው ሥር ትምህርት እየመሠረቱ ግዳጃቸውን ተወጥተዋል ።

አሁንም በመወጣት ላይ ናቸው ። የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት ስለ ኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ብዛት እንደ እ.አ. በ64 ዓ.ም. ባወጡት ዓመታዊ መጽሔታቸው 32.5% እንደ ሆነ ገምተዋል ።

በከተማና በገጠር ያሉት ካህናቶቻችንም ቁጥራቸው ከ200.000 በላይ እንደሆኑ አብያተ ክርስቲያናቱም ቁጥር ከ18000 በላይ እንደሆነ ይነገራል ፣ ታዲያ በኅብረ ሰባዊት በምትመራው በኢትዮጵያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ይህን ያህል ካህንና ሕዝብ ሲኖራት ፣

እንደሌሎች በኅብረተ ሰባዊት በሚመሩት ሀገሮች መካከል እንዳሉት አብያተ ክርስቲያናት በሰበካ ጉባዔ በሚገባ ተደራጅታ ብትመራ የተዝረከረከው አመራሯ ቅልጥፍና ያገኛል እላለሁ እውነተኛ ልጆቿም ቢታዛዋ ሆነው የበይ ተመልካች ከመሆን አልፈው ራሳቸውን ከችግር አዘቅት አውጥተው ሌላውን ከችግር አዘቅት የወደቀውን የሚረዱበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።

ይህን ያህል ካህንና ተከታይ ያላት ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ሰበካ ጉባዔ ፣ ስለሀገር ልማት ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ፣ ስለወንጌል መስፋፋት ፣ ዕቅድ አውጥታ ወደ ሥራ ብትሠማራ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከደረሱበት ደረጃ ትደርሳለች ብዙ ደቀ መዝሙራትም ባባቶች እግር ይተካሉ ለዚህም አመችይሆን ዘንድ የከተማ ካህናት ከገጠሩ ካህናት ብዙ ሊማሩና እንደነሱም ለሥራ ሊሰለፉ ይገባል እንላለን ። አስተርአየ ጽጌ

## ሥራና እምነት

ከ፲፱ኛው ገጽ የዞረ

መታዘዝ ከኃጢአት እንቅፋት ነጻ መውጣት ፣ ከሰብአዊ መጥፎ ስሜትና ዝንባሌ መዳን ነው በዕምነት ሰው የራሱ የመጥፎ ዝንባሌውና የመንፈሳዊ ጨለማ ሥልጣናት አሸናፊ ሊሆን ይችላል ኤፌ. 6፣12

በሥራችን ደግሞ እነዚህን ለመፈጸም ግን ምክር ወይንም አማኞች ነን ብለን በዕምነት ድንጋይ ዳቦ ይሁን ብንል ስለማይሆን በሕይወታችን በኩል ውድቀት ይመጣል ።

እነዚህን ልንነጣጥላቸው የማይገቡ የሕይወት መሪ የሆኑ ሕጐች ስለሆኑ አንዱን ልንጥል ሌላውን ግን ልንይዝ ብንሞክር የሕይወታችን አቋም በዕድሜያችን ሁሉ ሲያሳዝነን ይኖራል ።

ሥራ ያለዕምነት ዕምነትም ያለ ሥራ የሞተ ነውና ። ንብረት አበበ

## ልማድ ሃይማኖት አይደለም

ከ፲፱ኛው ገጽ የዞረ

ማለት ብቻ አይበቃም በሥራችን እውነተኞች ሃይማኖተኞች ሁነን መገኘት አለብን ።

ሃይማኖተኛዋ ሴት ስትወልድ ህፃኑ አጠገብ ቢላዋ ታስቀምጣለች ይህ ግዑዝ ቢላዋ ልጇን እንዲጠብቅ ነው ወይንስ ህፃኑ ሲንፈራገጥ በህፃኑ ላይ አደጋ እንዲያደርስ ? ይህችስ ሴት የሃይማኖታውያንን ሥራ ሰራች ማለት ይሆን ? መቸም ካለ ማወቅና ካለ መጠየቅ የምንፈፅማቸው ሃይማኖት መሰል መጥፎ ልማዶች አጥፊያችን እንጂ አልሚያችን አይደሉም ። ነፍስ የሌለውንና ይህን ዝቅተኛ ቢላዋ ነፍስ ያለውና እንዳውም ከእግዚአብሔር በላይ አድርገን የምንቆጥረው ካለማወቅ ይሆን ? ወይንስ የመጥፎ ልማድ ተገዥነታችን አልለቅ ብሎን?

ዴከርት የተባለው የፈረንሳይ ፈላስፋ ሲናገር "ያለ እግዚአብሔር በቀር ማንኛውም በዓለሙ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ፍጡር (ተፈጣሪ) ነው ። ይህውም እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ አሁን ካለው ሁሉ አንድም ነገር በራሱ ኃይል ሊፈጠር ባልቻለ ነበር ሲል ተናግሯል ።

አዎን ፍጡርንና ፈጣሪን መለየት አለብን ከሁሉም በፊት ፍጡር ለራሱ ፍጡር እንጂ ፈጣሪ ሊሆን የማይችል መሆኑን ማመን አለብን ።

ዛሬ ሁላችንም ካለማስተዋላችን የተነሣ ማንኛውም ነገር ትክክለኛና እርግጠኛ አድርገን እናስበው ይሆናል ። ነገር ግን ይህ አስተሳሰባችን ስህተት መሆኑ የምናውቀው ችግር አጋጥሞን ስናነጋግረው ለችግራችን መልስ ሰጭ ስናጣ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ።

ይህ ዓለም በአንድ ሃያል አስገኝ የተገኘ ወይም የተፈጠረ እንጂ ሰዎች በመጥፎ ልማድ አማካኝነት ከሚያመል

ተከታዩን በ፳፱ኛው ገጽ ይመልከቱ



## "ወላጆች ልጆቻችሁን በሥነ ሥርዓት አሳድጉ"

እግዚአብሔር አምላካችን ለሰው ልጆች የሥጋና የነፍስ መመሪያዎች ሆነው እንዲያገለግሉ አሥር ትእዛዛትን ለሙሴ ካስተማረ በኋላ በመጨረሻ "እሥራኤል ሆይ ስማ አምላክህ አንድ እግዚአብሔር ነው እርሱን በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ በፍጹም ልብህ ውደድ ፣ እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው" በማለት ለሙሴ ነግሮታል (ኦሪ ዘጸ 6፣4)

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸው የፍቅር ግንኙነት በተፈጥሮ የሚገኝ አምላካዊ ስጦታ በመሆኑ ማንም ሰው ተመራምሮ ሊደርስበት አይችልም እግዚአብሔርም ትእዛዛቱን ከሰጠ በኋላ በመጀመሪያ ለልጆችህ አስተምረው ማለቱ ከልጅ የሚቀርብ ሌላ አለመኖሩን ሲያስረዳ ነው ።

ይሁን እንጅ ልጆችን በሥነ ሥርዓት አሳድጎ ለቁም ነገር ማብቃት ለሀገር ማበርከት ብዙ ድካም ይጠይቃል ፣ ለምሳሌ አንድ ተክል መልካም ፍሬን ሊሰጥ የሚችለው በመሬቱ ላይ በመተከሉ ብቻ አይደለም የተተከለው ተክል መልካም ፍሬን እንዲሰጥ ከተፈለገ ከቡቃያው ጀምሮ መኮትኮት አፈር ማስታቀፍ ውሃ ሲያስፈልገውም ማጠጣት እንዲሁም ከከብት ከአውሬና ከልዩ ልዩ ተባይ መጠበቅ ያስፈልጋል ።

በዚሁ አንፃር የሰው ልጅም አድጐና ጐልምሶ ራሱን ችሎ ለወገኑና ለሀገሩ ከፍ ያለ ጥቅምን እንዲያበረክት ከተፈለገ ከሕፃንነቱ ጀምሮ በምግብ በልብስ በጤና በግብረ ገብነት እየተንከባከቡ ማሳደግ ተገቢ ነው ።

አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን በሥነ ሥርዓት ተንከባክበው ሳያሳድጉ ልጆችም የወላጆቻቸውን ፍቅር ሳያውቁ ጤናቸው ሳይጠበቅ የምግብ የልብስ የሞራል እርዳታ ሳይደረግላቸው በራሳቸው ጥረት ብቻ ተፍጨርጭረው ካደጉ በኋላ እንዲረዷቸውና እንዲጦሯቸው ይፈልጋሉ ። ልጆችም ተገቢው እንክብካቤ ሳይደረግላቸው በማደጋቸው ወላጆችን አንረዳም አንጦርም ያሉ እንደሆነ ይረግሟቸዋል ፣ ክርስታችንም እንዳትከፈሉ ከደናችኋል ከማለት ይደርሳሉ ። ይህም የልጆች ሳይሆን የወላጆች ጥፋት መሆኑ እያጠራጥርም በምግብ በልብስ በሞራልና በመሳሰሉትም ተንከባክቦ ያላሳደጉትን ልጅ እርዳኝ ጡረኝ ብሎ መጠየቅ ያላሳደጉትን የውሻ ጆሮ ለመጨበጥ እንደመቃጣት ያለ ሞኝነት ነው ።

ይህ እንዳይሆን ወላጆች ልጆቻቸውን ተንከባክቦ የማሳደግ ኃላፊነት እንዳለባቸው በቅድሚያ መገንዘብ አለባቸው ። በድሮው አስተሳሰብ የተመረዙ አንዳንድ ወላጆች "ልጅ በድሉ ያድጋል" የሚለውን ቃል መጠቃቀሳቸውን አልተውም ነገር ግን ይህ አነጋገር ስሕተት በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ለዕድል ብቻ ሰጥተው ከኃላፊነት ነፃ ሊሆኑ አይገባም ።

ምን ጊዜም ቢሆን የበለጠውንና እጅግ በጣም ያማረውን ነገር ለልጆቻቸው የማይመኙ ወላጆች በዓለም ላይ አይገኙም ስለዚህ ከሕፃንነታቸው ጀምረው በሞራል በልብስ በምግብ በጤናና በመሳሰሉት ነገሮች ተንከባክቦ የማሳደግ ግዴታ አለባቸው ። ልጆች ከትምህርታቸው ክፍል አብዛኛውን በቤታቸው ውስጥ የሚያገኙት መሆናቸውን ወላጆች ማወቅ ይኖርባቸዋል አንዳንድ ወላጆች ልጆቻችን መጥፎዎች ናቸው ነገር ግን ወደ ትምህርት ቤት አስገብተን አስተማሪዎች ልክ ያገቡልናል ይሉ ይሆናል ይህም አስተሳሰብ ትክክል አይደለም ፣ ይህንን ከማለት ይልቅ ልጆችን ራስ ሠርቶ ቀጥቶ ማሳደጉ ጠቃሚ ይሆናል ።

ጠቢቡ ሲራክ ስለ ወላጆችና ልጆች በተናገረበት አንቀጽ ሲገልጽ "ልጁን የሚወድ ሰው በእርሱ ደስ ይለው ዘንድ ልጁን መቅጣትን ቸል አይበል ልጁን ያስተማረ ሰው በልጁ መናገር ያመሰግኑታል በወዳጁም ዘንድ መመኪያ ይሆናል" ብሏል መ. ሲራክ 30፣1-2

ሐዋርያው ጳውሎስም ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ 6፣1-4 "ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር እርሷም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት" ይልና እናንተም ወላጆች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣፅ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው"

ብሏል ።

ወላጆች ልጆቻቸውን በሚገባ ካላሳደጓቸው ልጆችም የወላጆቻቸውን ምክርና ተግሣጽ እየተቀበሉ ካላደጉ ሁሉም ለሀገርና ለወገን ሸክም ይሆናሉ ።

በአንዳንድ የሶሻሊስት ሀገሮች ያለውን የወላጆችንና የልጆች ሁኔታ ብናስታውስ ጠቃሚ ትምህርትን ለመቅሰም ያስችለናል ፣ በአሁኑ ጊዜ በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር የሚመሩ በርካት ያሉ አህጉር በዓለም ላይ መኖራቸው የሚያከራክር አይደለም ። እነዚህ የሶሻሊስት ሀገሮች ሥርዓተ ትምህርታቸው በፊት ከነበራቸው ሥርዓተ ትምህርት ጋር ተመሳሳይነት የለውም የሶሻሊስት ሥርዓት ከመመሥረቱ በፊት ቤተ ክርስቲያንም የግብረ ገብ መምህራንን በየትምህርት ቤቶች እየላከች የማስተማር ግዴታ ነበረባት የሶሻሊስት መንግሥት ከተመሠረተ ወዲህ ግን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርቷን ለይታ የግል ትምህርት ቤቶቿን ከፍታ ፣ ሊቃውንቶቿን ሰብስባ እንድታስተምር መንግሥት ነፃነትን ሰጥቷታል ።

ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል እንደ ነበረው ሥርዓት በየትምህርት ቤቶች እየሄደች የማስተማር ሥልጣን ባይሰጣትም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የማስተማር ሥልጣን አልተነፈጋትም ። ስለዚህም ጋዜጦችን መጽሔቶችን እንዲሁም ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እያሳተመች ለምዕመናኑ ታቀርባለች ።

ወላጆችም ለልጆቻቸው የግብረ ገብ አስተማሪዎች መሆናቸውን በመገንዘብ መንፈሳውያን መጻሕፍትን ጋዜጦችንና መጽሔቶችን በመግዛት ራሳቸው እንብበው ልጆቻቸውም እንዲያነቡ ያደርጋሉ ።

በሶሻሊስት ሀገር በዚህ ረገድ ሃይማኖታቸውን ፣ ባህላቸውን ሥርዓታቸውን ልማዳቸውን ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣውን ታሪካቸውን ወላጆች በቤታቸው ለልጆቻቸው ስለሚያስጠኗቸው ወጣቶቹ ሁሉ በሞራል የታነጹ ሲሆኑ ሃይማኖታቸውም የጠነከረ ሥነ ምግባራቸው ያማረና የተወደደ ሆኖ ይገኛል አብዛኞቹ ወጣቶች ስለ ወላጆቻቸው ስለጐረቤቶቻቸው ስለሀገራቸው ከዚያም አልፈው ተርፈው ስለዓለም ሕዝብ ያላቸው አስተሳሰብ ፍቅርንና ርኅራኄን የተሞላ ሆኖ ይገኛል ።

በሶሻሊስት ሀገር ወላጆች ለልጆቻቸው ብዙ ጥንቃቄዎችን ያደርጉላቸው ከሚያደርጉላቸውም ጥንቃቄዎች አንዱ በልጆች መካከል እርስ በእርስ አለመጣላት አለመጨቃጨቅና አለመነታረክ ነው ፣ በወላጆች መካከል አንዳንድ ጊዜ አለመግባባት ሲፈጠር ከልጆች ለየት በማለት ክርክራቸውን ይፈጽማሉ ከዚህም የተነሣ ልጆች ከወላጆችም ጋር ሆነ ከጓደኞቻቸው ጋር መጨቃጨቅንና መነታረክን በፍጹም አያውቁም ።

አንዲት የቤት እመቤት ጓደኛዋን "ልጆቹ ምንም አስቸግረውኝ አያውቁም" ብትላት "ከባልሽ ጋር በደስታና በሰላም ብትኖሩ ነው" አለቻት ይባላል ።

በእርግጥ የወላጆች እርስ በርስ አለመስማማት ልጆችን ወደ ስሕተት መንገድ የሚመራቸው



www.ethiopianorthodox.org

## ልማድና ሃይማኖትን ለይቶ ማወቅ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው ። ልማድ ይሻሻል ። ሃይማኖት ግን የማይለወጥና የማይሻሻል ሕግ ነው ።

## ወላጆች ልጆቻችሁን

ሲሆን መፋቀራቸው ደግሞ ወደ ደስታ እንዲያ ዘነብሉ ያደርጋቸዋል ለሚያድግ ቡቃያ የፀሐይ ብርሃን እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለሚያድጉም ሕፃናት መልካም አርያነት ያላቸው ወላጆች ተፈላጊዎች ናቸው ።

አንድ ሊቅ ሲናገር "ትንንሾች ልጆችን በእጃችን እንዳለ ሰም ናቸው አዳዲስ ዘዴና ሐሳብ ለመቀበል በቂ ማስተዋልና ትሕትና ቢና ረን ጥሩዎችና ጠንካራዎች እንዲሆኑ ልንቀርጻ ቸው እንችላለን" ብሏል ነገሩ የሚታበል አይደ ለም በቅሉ እንደገሪው ወይፈን እንደ አቅኑ የሚራመድ እንደሚሆን ሕፃናትም በለጋነታ ቸው ያስያዟቸውን አይለቁም ።

በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሶሻሊስት ን አሠራር ፍኖት ይዛ በመራመድ ላይ ትገኛለች በዚህ ወቅት ልጆችንም መንከባከብ ያለባት በሶ ሻሊስት መንፈስ ነው እስከ ቅርብ ቀን ድረስ በሀገራችን ወላጆች ስለልጆቻቸው ግብረ ገብ ነት ስለልጆቻቸው የትምህርት ሁኔታ አያስ ቡም ነበር ይህንንም የሚያደርጉት በየትምህ ርት ቤቶች በርከት ያሉ የግብረ ገብ አስተማሪ ዎች በመኖራቸው ሐሳባቸው በእነርሱ ላይ በመጣል ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ ግን ግብረ ገብ አስተማሪ ዎች እያሱ በመሄድ ላይ ናቸው ፤ እንግ ዲህ ወዲህ እንደ ግብረ ገብ አስተማሪዎች ሆ ነው ልጆቻቸውን በጢት በማታ መቆጣጠር ያ ለባቸው ወላጆች ናቸው ልጅን መውለድ ብቻ በቂ አይደለም ከወለዱም በኋላ በምግብ በልብስ በጤናና በሞራል ተንከባክቦ አሳድጐ ለወገንና ለሀገር መልካም ዜጋ አድርጐ ማቅረብ ይገባል፡

ልጆች ያላወቁትን እንዲያውቁ ያልተማሩ ትን እንዲማሩ ባህላቸውን እንዲያከብሩ እምነ ታቸውን እንዲያጸኑ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር እንዲያድርባቸው የማድረግ ኃላፊነት ያለ ባቸው ወላጆች ናቸው ይህንን ቃል ያዝ ለልጆ ችህም አስተምረው እንደተባለው ማንኛችም ወላጆች ራሳቸው አውቀውና ተረድተው ልጆ ቻቸውንም የማሳወቅና የማስረዳት ግዴታ እንዳ ለባቸው ሊገነዘቡት ይገባል ።

ቄስ ልሳነወርቅ በዛብህ

## ልማድ ሃይማኖት አይደለም

ከ፰ኛው ገጽ የዞረ

ኳቸው ነገሮች (ፍጡሮች) የተፈጠረ ያለ መሆኑን መገንዘብ ግዴታችን ነው፤

በአሁኑ ጊዜ የሚፃፈው ሃይማኖት ነክ ትምህርት ሁሉ ለቀልድ ፣ ለጨዋታ ወይም ለተወሰነ ቀን ሳይሆን ይህ መ ጥፎ ልማድ ከሥሩ ተመንግሎ እንዲ ጠፋ ለዘሌቄታ መሆኑን እንወቅ ሁላች ንም ምዕታችንን ህብረተሰቡ ከአጉል ልማድ ተላቆ እውነተኛ ሃይማኖቱን ለይቶ አውቆ ለሃገሩና ለወገኑ ኩራት ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚያስብ እውነተኛ ህብረተሰብ እንዲሆን መሆን አለበት ይህም ለተርእዩ ሳይሆን ሃገራ ችንና ሃይማኖታችንን የሚያስቀድም በሥራ የተገለጠ አማናዊ ቃልና ሥራ መሆን አለበት ።

ብርሃን ተድላ

## የሠራተኞች ኃይል ....

ከ፲፫ኛው ገጽ የዞረ

ስለዚህም ጌታ ክርስቶስ "የመጀመ ሪያው የመጨረሻ የመጨረሻም የመጀ መሪያ ይሆናል" ሲል ተናግሮአል ይህ ም በሥራ እንጂ በስም መቅደም የመጀ መሪያ ደረጃ እንደማይገኝ ያብራራል ። እሱም ቤተክርስቲያንን የመሠረታት ኑሮአቸውን አሻሽለው ጣባያቸውን አሳ ምረው የሚኖሩትን ጻድቃን እንድታስ ተምር ብቻ አይደለም ይህ ቢሆን ኑሮ "ኃጥአንን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አል መጣሁም" ሲል ባላስተማረም ነበር በተጨማሪም በሠራተኛ ደመወዙ ይገባ ኑሮአቸውን ጣጠባያቸውን አሳምረው የሚኖሩትን ፃድቃን እንድታስተምር ብቻ አይደለም ይህ ቢሆን ኑሮ ኃጥአንን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም" ሲል ባላስተማረም ነበር በተጨማሪም በሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል ባላለም ነበር ።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋ ዮች የሆኑ ሁሉ በቃሉ መሠረት የክስ ዶሴአቸውን ዘግተው የወንጌልን ብር ሃን ለሌሎች ያብሩ ራሳቸውም የሰላም ሰዎች ሁነው ሰላምን አጥተው ለሚቅ በዘበዙ ሰላም ይስበኩ ቤተ ክርስቲያን ም የሰላም መድረክ እንድትሆን ራሳቸ ው ታፈቂ ሁነው ሌሎችን ያስታርቁ ።

ሕዝብም በብዛት በሚገኝበት ሥፍራ እየተገኙ የችግሩን የደስታው ተካፋይ በመሆን ድህነት ፣ በሽታ ፣ ድንቁርና እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ በ ሚጠፉበት መንገድ ሁሉ የሥራው ተ ባባሪ ይሁኑ ይህን ካደረጉ ቤተ ክርስቲ ያንም የስም ሳይሆን የሥራ ቤተክርስ ስቲያን ትሆናለች ወጣቶች ሸሹ ያሳደግ ኳቸው ልጆች ጥለውኝ ሄዱ ። ከማለ ትም ትድናለች ።

በዚህ አኳኋን ማንኛውም ሰው ከረ ዱት ፣ አስተምሮ የሥራ በር ከከፈቱ ለት እንኳንስ የራስ ልጅ የሌላውም ልጅ ቢሆን የገዛ ልጅ ልጅ ሊሆን ይች ላል አውሬው እንኳን ሳይቀር ለማዳ ሁኖ ይቀርባል ነገር ግን ካልረዱት ፣ የሥራ መንገድ ካልከፈቱለት የራስም ልጅ ቢሆን የእንጀራ ልጅ ይሆናል ።

ስለዚህም ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ልትወጣውም የምትችለው የሠራተኛ ቿ ኃይል ያልተከፋፈለ እንደሆነ ነው ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን ለእግ ዚአብሔር ፣ የቄሣርን ለቄሣር የሕዝ ብን ለሕዝብ መሥራት እንድትችል ኃይሏን ታስተባብር "እርስ በርሷ የም ትለያይ ቤት አትፀናም ትፈርሳለች" ተብሎ ተጽፎአልና ።


## ማሳሰቢያ

1ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት "ድምፀ ተዋሕዶ" የተሰኘ ጋዜጣ ከአሁን በፊት ለ14 ዓመታት ያህል እያሳ ተመ ለምእመናን እንዲዳረስ ሲያደርግ ቆይቷል ።

አሁን ግን በይበልጥ ከመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ጀምሮ በማኅበርተኝነ ትም ሆነ በበዓላት ቀን ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚዳረስበትን መንገድ በማጥናት ላይ ስለሆነ ይህንን ማሳሰቢያ የሚያነቡ ሁሉ አስተያየታቸውና ትብብራቸው እንዳ ይለየው ያሳስባል ።

2ኛ መንፈሳውያን መልእክቶችን መንፈሳውያን የሆኑ ዘመናውያን መዝሙሮች ንና ጥንታውያን ዜማዎችን በካሴት እየቀረፀ ካሴት ለማያቀርቡ የካሴት ዋጋ 55 የአገልግሎት ደግሞ 2 ብር ብቻ እያስከፈለ የሚሰጥ መሆኑን በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣችን ማሳሰባችን ይታወሳል ።

አሁንም በዚሁ ሁኔታ የቀጠለ መሆኑን እንገልጣለን ።



አድራሻችን አራት ኪሎ ብሔራዊ ሸንጎ ፊት ለፊት
የስልክ ቁጥር 11 - 66 - 15
የፖ.ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org